ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 214 ሚያዝያ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስዎች ያወጡት ሪፖርት ከመረጃ አሰባሰቡ እስከ ውጤቱ ለአንድ ወገን ያደላ ነው

- አምባሳደር ዲና ሙፍቲ



ፍቃዱ ዴሪሳ

አዲስ አበባ፡- ከሰሞኑ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች በጋራ በመሆን ኢትዮጵያን በሚመለከት ያወጡት ሪፖርት ከመረጃ አሰባሰቡ እስከ ውጤቱ ለአንድ ወገን ያደላ መሆኑን የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ገለፁ።

አምባሳደር ዲና በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ ተቋማቱ መሬት ላይ የሚታዩና በርካታ መረጃዎችና ሁኔታዎችን በተገቢው ሁኔታ ሳይከታተሉ እንዲሁም ተገቢውን የማጣራት ሂደት ሳይከተሉ ለአንድ ወገን በማድላት ሌላኛውን ደግሞ በመኮነን ሪፖርት አውጥተዋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች በጋራ በመሆን ያወጡት ሪፖርት ወገንተኛነታቸውንና ጭፍን አቋማቸውን ያራመዱበት ሪፖርት ትክክል አለመሆኑን የተናገሩት አምባሳደር ዲና፣ የአማራ ክልል መንግሥት ይህን በሚመለከት ያወጣው መግለጫ ተገቢነት ያለው መሆኑን ተናግረዋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናልና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «የእስካሁኑ ጥፋት ይብቃ፤ ከአሁን በኋላ ችግሮቻችንን በምክክር እንፍታ»

- ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጂ ዑመር ኢድሪስ



ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- እስካሁን የጠፋው ጥፋት ይብቃ ከአሁን በኋላ ችግሮቻችንን በምክክርና በውይይት እንፍታ ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጂ ዑመር ኢድሪስ ገለፁ። ተቀዳሚ ሙፍቲው አገርን ለማስቀጠል የአገራዊ ምክክሩ ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነም ተናግረዋል።

ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጂ ዑመር ኢድሪስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ እስካሁን የጠፋው ጥፋት ይበቃል በማለት ፊትን ወደ ሰላም ማዞር ይገባል።

አገርን ለማስቀጠል የአገራዊ ምክክሩ ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ ምክክሩ እኩልነት በሰፈነበት፤ በእውነትና በአንድነት መንገድ የሚከወን ከሆነ ለአገራችን አወንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

መመካከርና መወያየት የቆየ የኢትዮጵያውያን ትውፊት እንደሆነ ያወሱት ሃጂ ዑመር፤ በመመካከርና በመወያየት ችግራችንን ልንፈታ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

«የእስካሁኑ ጥፋት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














## ሕዝብና መንግሥት በቅንጅት በሠሩባቸው አካባቢዎች በሽኔ ላይ ድል መገኘቱን የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ

ገጽ 4







# ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በጤናው ዘርፍ በትብብር ለመሥራትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን ገለጸች

አዲስ አበባ፡- በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ከቻይና የበሽታዎች መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ማዕከል (ሲ ዲ ሲ) ዳይሬክተር ጉው ፉ ጋር በበይነ መረብ ተወያይተዋል።

በውይይታቸውም ሁለቱ አገራት በተለይ በበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ረገድ በትብብር መሥራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል።

አምባሳደር ተሾመ ኢትዮጵያና ቻይና ያላቸውን ዘርፈ ብዙ ትብብርና ግንኙነት በውይይቱ አንስተዋል።

አገራቱ በሕክምናው ዘርፍ የሚያደርጉትን ትብብር አሁን ካለበት ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በሁለቱም ወገን ከፍተኛ ፍላጎት ያለ መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህም የቻይናው ሲዲሲ ከኢትዮጵያ አቻ የሕክምና ተቋማት ጋር በሰው ኃይል አቅም ግንባታ፣ በጥናትና ምርምር ተቋማት ጉድኝት፣ በፋርማሲዩቲካል ኢንቨስትመንትና በሕክምና ቴክኖሎጂ ልውውጥ በቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረም ማዕቀፍ ተባብረው እንዲሠሩ ጠይቀዋል።

አምባሳደር ተሾመ አያይዘውም በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ በተከሰተው ጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው የሕክምና ተቋማት የመድኃኒትና የሕክምና መርጃ መሣሪያዎችን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።



ጉው ፉ በበኩላቸው፣ ቻይና እና ኢትዮጵያ በሕክምናው ዘርፍ ጠንካራ ትብብር ያላቸው አገራት መሆናቸውን አንስተዋል።

በተለይ የአፍሪካ ሲዲሲ በአዲስ አበባ እየተገነባ መሆኑ የቻይና የበሽታዎች መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ማዕከል ከአፍሪካ አገራት ጋር በሕክምናው ዘርፍ ለሚያደርገው የትብብር ሥራ ኢትዮጵያን ማዕከል አድርጎ ለመጠቀም ምቹ ዕድል የሚፈጥርለት መሆኑን ተናግረዋል።

አምባሳደሩ ባቀረቧቸው ጉዳዮችና በሌሎችም ተያያዥ ዘርፎች ላይም በጋራ ለመሥራትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆኑ መግለጻቸውን ከቻይና የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።



# አቮካዶን ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ አመታት ወዲህ የአቮካዶ ተክልን በማስፋትና ምርታማነትን በመጨመር ከአገር ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየተሠራ መሆኑ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የሆልቲ ካልቸር ልማትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር አቶ አብደላ ነጋሽ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አርሶ አደሩ ጥራት ያለው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትና ተፈላጊነት ያላቸው የአቮካዶ ዝርያዎችን እንዲያገኝ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው። የአቮካዶ ምርትን ወደ ውጭ ለመላክ በአሁኑ ሰዓት የሀስ ዝርያ በከፍተኛ ሁኔታ እየተባዛ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የአቮካዶ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በአምስት የችግኝ ማባዣ ማዕከሎች የአቮካዶ ችግኞች እየተባዙ ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ ሲደረግ ቆይቷል። ነገር ግን የሕዝቡ ፍላጎት በመጨመሩ ውስን የነበሩ የችግኝ ማባዣ ማዕከላትን በማስፋት የአቮካዶ ችግኝ እንደ አገር በስፋት እንዲዳረስ እየተሠራ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ 50 በሚደርሱ የችግኝ ጣቢያ ማዕከላት ችግኝ የማባዛት ሥራ እየተሠራ ነው። የአቮካዶ ዝርያን ለማዘመን በግብርና ትራንስፎርሜሽንና ከሌሎች አጋር አካላት እየተሠሩ ያሉ በርካታ ሥራዎች መኖራቸውንም ገልጸዋል።

ሌሎች የአቮካዶ ዝርያዎች በስፋትና በትኩረት እየተባዙ ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አብደላ፤ አግሮ ኢንዱስትሪው የሚፈልጋቸው ከፍተኛ የዘይት መጠን ያላቸው ዝርያዎች እየተባዙ ነው።

አገራዊ የሆኑ ዝርያዎችን አርሶ አደሩ በራሱ እያባዛ የሚሠራበት ሁኔታ መኖሩን አብራርተዋል። ለአርሶ አደሩ በተቻለ መጠን ተፈላጊ የሆኑ ዝርያዎችን በስፋት እንዲሠራ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

# በስቶክሆልም ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ጠንካራ አገራዊ አቋም ይዞ ለመቅረብ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በመጪው ሰኔ ወር በስዊድን ስቶክሆልም በሚካሄደው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ጉባኤ ላይ ጠንካራ አገራዊ አቋም ይዞ ለመቅረብ እየተሠራ መሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ።

የኢፌዴሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ጌታሁን ጋረደው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በስቶክሆልም ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ጉባኤ ላይ ልምዳቸውን ከሚያካፍሉ 58 አገሮች አንዷሆና ተመርጣለች። በዚህም ከአየር ንብረት ጋር የሚገናኙ ሥራዎችን ከሚሠሩና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ በጉባኤው ላይ ጠንካራ አገራዊ አቋም ይዞ ለመቅረብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በአገራት ላይ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት ለችግሩ ባበረከቱት መጠን አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የተወሰኑ የበለጸጉ አገሮች ወደ ከባቢ አየር በሚለቁት በካይ ጋዝ ሳቢያ የአየር ንብረት ለውጥ በሚያስከትለው ጦስ ሌሎች አገሮችም የገፈቱ ቀማሽ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

በስቶክሆልሙ ጉባኤ ላይ የአገሪቱን ልምድ፣ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የሕግ ማዕቀፎችንና የሚደርስባትን ጉዳትና ከጉዳቱ ለመውጣት ያላትን እቅድ የምታሳውቅበት መሆኑን ጠቁመው፤ ድርድሩን ተከትሎ በሚኖረው ማዕቀፋዊ ስምምነት አስገዳጅ ሥራዎችና ድጋፎችንም ስለሚያመጣ የሚደረገው ንግግርና ድርድር አገራዊ ምስል እንዲይዝ ይሠራል ብለዋል።



ዶ/ር ጌታቸው ጋረደው



ስቴፈን ሩስ

ከዚህ ቀደም እንደ አገር የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳቱን እንዴት እንቀንስ በሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ይደረግ እንደነበር አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ የፓሪስ ስምምነትን ከፈረመች በኋላ ግን ለአየር ንብረት ለውጥ ያለን ድርሻ ትንሽም ቢሆን ችግሩን ለማስቀረት የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል በሚል የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስችል እቅድ ማውጣቷን አብራርተዋል።

ጉዳቱን ለመቋቋም በሚደረገው ሂደት ውስጥ 20 በመቶ የሚሆነውን ገንዘብ ለብክለቱ ብዙም አስተዋጽኦ የሌላቸው አገራት ሲሸፍኑ 80 በመቶውን ለለውጡ ከፍ ያለ ድርሻ ያላቸው አገሮች መሸፈን አለባቸው የሚል ሀሳብ አቅርባ ተቀባይነት ማግኘቱንም ዶክተር ጌታሁን ጨምረው ገልጸዋል።

የአየር ንብረት ለውጥና ተያያዥ ችግሮችን በተናጠል በሚሠሩ ሥራዎች መፍታት አይቻልም ያሉት ዶክተር ጌታሁን፤ በዚህም የሁሉንም አገራት ትብብርና ያላሰለሰ ጥረት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

የስዊድን ኤምባሲን በመወከል መልዕክት ያስተላለፉት ስቴፈን ሩስ በበኩላቸው፤ ስዊድን የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ጥልቅ ሚና እንደሚኖረው የሚጠበቀውን የስቶክሆልም +50 የአየር ንብረት ጉባኤ እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ሁሉም አገራት በትኩረትና በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ የምንሠራቸው ሥራዎችና የምንወስዳቸው እርምጃዎች የተናበቡና ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሆኑ መግባባት ላይ መድረስ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የስቶክሆልም +50 የአየር ንብረት ጉባኤ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1972 ስቶኮልሆም ላይ የተቋቋመውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ፕሮግራም 50ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የሚካሄድ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ በጉባኤው ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ 58 አገራት ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ፣ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የሕግ ማዕቀፎችንና የሚደርስባቸውን ጉዳትና ከጉዳቱ ለመውጣት ያላቸውን እቅድ የሚያሳውቁበት ዕድል ተሰጥቷቸዋል ተብሏል።

# ‹‹ፍራንኮ ቫሉታን መፈቀዱ የዋጋ ግሽበቱን ለመቀነስና የምርት አቅርቦትን ለመጨመር ይረዳል››

- አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በመሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች ላይ ፍራንኮ ቫሉታን መፍቀዱ የዋጋ ግሽበቱን ለመቀነስና የምርት አቅርቦትን ለመጨመር እንደሚረዳ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ገለጹ።

አቶ ዘመዴነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት መሠረታዊ የምግብ ፍጆታን ለማስገባት በማሰብ ፍራንኮ ቫሉታ መፍቀዱ የዋጋ ግሽበቱን ይቀንሳል። በተመሳሳይ የአገር ውስጥ አቅርቦትን እንዲጨምር ያግዛል።

መሠረታዊ ፍጆታዎችን በባንኮች የገንዘብ አቅም ብቻ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት አለ ያሉት ባለሙያው፤ ይህም የምርት እጥረት አስከትሏል። እጥረቱን ለመቀነስ ፍራንኮ ቫሉታው መፈቀዱ ሰዎች በእራሳቸው የውጭ ምንዛሬ አቅም መሠረታዊ ፍጆታዎችን እንዲያስገቡ ይረዳል ብለዋል።

ይህም የአገር ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦትም አለመመጣጠን በማስተካከል፤ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትና የምርት እጥረትን ለመቅረፍ ጥሩ መፍትሄ ተደርጎ እንደሚታይም ነው አቶ ዘመዴነህ የተናገሩት።

ኅብረተሰቡ በየቀኑ የሚጠቀማቸው የምግብ ግብዓቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ እሙን ነው። ለዚህም የውጭ ምንዛሬ ሂደት ውስጥ ሳይገባ ምንጩ የታወቀ ዶላር በውጭ አገራት ያለው ያለው ነጋዴ ምግብ ነክ ነገሮችን እንዲያስገባ መፈቀዱ ጥሩ አካሄድ ነው ብለዋል።

አሠራሩ ያለውን ወቅታዊ ችግር በአጭር ጊዜ እንዲፈታ ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ፍራንኮ ቫሉታ አገር ውስጥ ያለውን የውጭ ምንዛሬ አይሻማም። አገር ውስጥ የገባው ምንዛሬ ለሌላ ነገር



እንዲውል ዕድል ይሰጣል ሲሉ አስረድተዋል።

በዚህ አካሄድ በውጭ ባንኮች ገንዘብ ያለው የፍራንኮ ቫሉታውን ዕድል መጠቀም ይችላል፤ በተለይም በብዛት ዳያስፖራው ይህን አጋጣሚውን በመጠቀም ምርቶችን ማስገባት አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሌሎች አገራት እንደሚያደርጉት የውጭ ምንዛሬ በተፈለገው ሁኔታ ማውጣትና ማስገባት ይቻላል ያሉት ባለሙያው፤ ኢትዮጵያ እዚያ ደረጃ ላይ ባለመድረሷ ፍራንኮ ቫሉታው የተፈቀደው በልዩ ሁኔታ ታይቶ ነው ብለዋል።

የምንዛሬ እጥረቱ ከሁለትና ሦስት ዓመታት በኋላ ሊቀየር ስለሚችል የውጭ ምንዛሬ የሚያድግበት ሂደት ይኖራል። በዚያን ጊዜ የፍራንኮ ቫሉታ አሠራር ላይተገበር እንደሚችል ይጠበቃል ሲሉም ተናግረዋል።

ኬንያ፣ ኡጋንዳና ታንዛኒያ የሚከተሉት የውጭ ምንዛሬ ቁጥጥር የለም። እንደፈለጉ ያስገባሉ ያስወጣሉ። አስመጪዎቹም ዶላር ከፈለጉበት የውጭ ባንክ አምጥተው ዕቃ ያስገባሉ ሲሉ የየአገራቱን ተሞክሮ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያም የውጭ ምንዛሬ ክምችቷ ሲሻሻል አንድ ቀን እዚያ ደረጃ ላይ ትደርሳለች። እስከዚያው ድረስ በልዩነት አሁን እንደተተገበረው ዓይነት የፍራንኮ ቫሉታ አሠራርን መተግበሯ ተገቢ ነው ብለዋል።

ፍራንኮ ቫሉታ ጊዜያዊና የአጭር ጊዜ ፈጣንና ምላሽ ሰጪ መፍትሄ ነው። አሁን ያለውን ወቅታዊ ችግር በአጭር ጊዜ እንዲፈታ ታስቦ የተፈቀደ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደአቶ ዘመዴነህ ገለጻ፤ የአገርን የውጭ ምንዛሬ አቅምን የሚያሳድግ በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ከዚህ ባለፈ ግን የምርት እጥረቱን ለመቀነስ የአገር ውስጥ ተኪ ምርቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል ብለዋል።

የምግብ ፍጆታ እጥረት ሲያጋጥም ዋጋ እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ነው ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ ይሄ ደግሞ ግሽበት እንዲፈጠር ያደርጋል ሲሉ ባለሙያው ተናግረዋል።

በርካታ ችግሮችንም ይፈጥራል። ሆኖም ግን በቀጣይነት የአገር ውስጥ ምርትን በማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን መቀነስ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለመፍትሔውም በቋሚነት የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህም ከውስጥ ፍላጎት አልፎም የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምርቶችን በስፋት ማምረትና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይጠይቃል ብለዋል።

ለዚህም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ የሚያስችል እስትራቴጂ ሊተገበር እንደሚገባ አሳስበዋል።



# ኢትዮ ቴሌኮም የኢንተርኔት አገልግሎትን ለማስፋፋት ከአጋሮቹ ጋር በጥምረት እንደሚሠራ ገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎትን ለማስፋፋት ከአጋሮቹ ጋር በጥምረት እንደሚሠራ ገለጸ። ኩባንያው ከአምስት ባለገመድ ኢንተርኔት አገልግሎትን በአጋርነት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር የስምምነት ውል ተፈራርሟል።

የኢትዮ ቴሌኮም ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ ኩባንያቸው ትናንት ባለገመድ ኢንተርኔት አገልግሎትን በአጋርነት ከሚሰጡ አምስት ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ሲያደርግ እንደገለጹት፤ የብሮድ ባንድ አገልግሎት መስፋፋት አገራችን ለምትገነባው የዲጂታል ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። ይህንንም አገልግሎት ይበልጥ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ከአጋሮቻችን ጋር በጥምረት እንሠራለን።

ከሦስት ዓመት በፊት 66ሺህ ብቻ የነበረው የባለገመድ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር አሁን 479ሺህ በላይ መድረሱን ወይዘሪት ፍሬሕይወት አመልክተው፤ ኩባንያው እኤአ በ2026 የመደበኛ ኢንተርኔት ተጠቃሚዎቹን ቁጥር ሦስት ሚሊዮን ለማድረስ እቅድ መያዙን አመልክተዋል።

ይህን እቅዱን ለማሳካትም የተለያዩ መጠነ ሰፊ አሠራሮችንና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ትግበራ ላይ እንደሚገኝም ጠቁመው፤ ኩባንያቸው በትናንትናው ዕለት ከአምስቱ ድርጅቶች ጋር የተፈራረመው ስምምነት የመደበኛ ብሮድባንድ አገልግሎትን ለደንበኞቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችለው መሆኑን አስታውቀዋል።

ኩባንያቸው ከሞባይል ኢንተርኔት በተጨማሪ በመደበኛ ባለገመድ ኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋፋት በራሱ እያከናወነ ከሚገኘው ሥራ በተጨማሪ የአጋር ድርጅቶቹ ሚና ከፍተኛ አቅም የሚፈጥር እንደሚሆንም ተናግረዋል።

አጋር አካላቱ ተፎካካሪ ያለመሆናቸውን የገለፁት ወይዘሪት ፍሬሕይወት፤ ስምምነቱ ያለውን ውስን ሀብት በጋራ ለመጠቀም ያስችላልም ብለዋል።

በስምምነቱ መሠረት ድርጅቶቹ የመደበኛ ኢንተርኔት ከፍተኛ «ባንድ ዊድዝ»ን ከኢትዮ ቴሌኮም በመውሰድ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ለሚገኙ ደንበኞች ያደርሳሉ ያሉት ወይዘሪት ፍሬሕይወት፤ የኢትዮ ቴሌኮም ደንበኞች ከሽያጭ ማዕከላቱ በተጨማሪ ከተጠቀሱት አምሥት ድርጅቶች የመደበኛ ኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉም ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም እና አምሥቱ አጋር ድርጅቶች የተፈራረሙት ሥምምነት ለሦስት ዓመታት የሚቆይ መሆኑም ተገልጿል። ኩባንያው በትናትናው ዕለትም ከስካይ ኔት አይቲ ሶሉሽን፣ ዘርጋው አይ ኤስ ፒ፣ ዌብ ስፕሪክስ፣ ቪቫ ቴክ ትሬዲንግ እንዲሁም ዱሌ ቢዝነስ ግሩፕ ከተባሉ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመሥራት ስምምነት ተፈራርሟል። ኢቲዮ ቴሌኮም ከ64 ሚሊዮን በላይ ደንበኞች እንዳሉት ለማወቅ ተችሏል።

# የሂዩማን ራይትስ ዎችና የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የጥናት ሪፖርት በትክክለኛ መረጃ የተደገፈ አይደለም

አዲስ አበባ፡- የሂዩማን ራይትስ ዎችና የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የጥናት ሪፖርት በትክክለኛ መረጃ የተደገፈ አለመሆኑን የባልሲሊ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ምርምር ተቋም ዳይሬክተር አን ፊትዝ ጄራልድ ተናገሩ።

በቅርቡ ተቋማቱ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተለይም በምዕራብ ትግራይ ተከስቷል ያሉትን የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመለከተ የጋራ ሪፖርት ማውጣታቸው ይታወሳል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሪፖርቱ የፖለቲካ ወገንተኝነትና በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የተንጸባረቀበት መሆኑን በመጠቆም ሪፖርቱን እንደማይቀበለው ገልጿል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተከሰተውን ጦርነት በቅርበት የሚከታተሉት ፕሮፌሰር አን ፊትዝ ጄራልድም የተቋማቱ ሪፖርት ትክክል አለመሆኑን ይናገራሉ።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ሪፖርቱ መሠረታዊ የጥናትና ምርምር አካሄድን የዘነጋና በዋናው የጥናት ክፍልና መደምደሚያ ላይ የተጠቀሱት መረጃዎች እርስ በርሳቸው መመጋገብ የማይችሉ ናቸው።

በተለይም በማጠቃለያና በምክረ ሃሳብ ላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ጥናቱ ዋናው የትንተና ክፍል ውስጥ በዝርዝር ያልቀረቡና ግንጥል ሪፖርት መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንዲህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ሲካሄድ የፎረንሲክ መረጃዎች የግድ መካተት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ተቋማቱ ጥናትና ሪፖርት ግን ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ መዘንጋቱን ገልጸዋል።

በተጨማሪም፤ ጥናቱን ያጠኑት ግለሰቦች ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ተፈጽሟል ያሉት ሥፍራ ተገኝተው ጥናቱን አለማካሄዳቸውም የጥናት ሪፖርቱ ሙሉ እንዳይሆን ማድረጉን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በጉዳዩ ላይ ጥናት አድርጎ ሪፖርቱን ለማቅረብ ሁለት ቀን ሲቀረው ተቋማቱ ሪፖርታቸውን ያቀረቡበት ሁኔታም ፖለቲካዊ ይዘት ሊኖረው እንደሚችል አመላክተዋል።

ያም ብቻ ሳይሆን እነዚህ ተቋማት ጎንደር ዩኒቨርሲቲን አለማማከራቸው ሌላኛው የጥናትና ምርምር ሥራቸው ጎደሎ ለመሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል።

ፕሮፌሰር አን ፊትዝ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን የተለያዩ አካባቢዎችን ባለፈው ሣምንት መጎብኘታቸውን ጠቁመው፤ መሠረተ ልማቶች በእጅጉ መውደማቸውን እንደተመለከቱ ተናግረዋል።

በተጓዳኝም በጦርነቱ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች ችግር ላይ በመውደቃቸው ለዜጎቹ የሚደረገው የሰብዓዊ ድጋፍ አሁን ካለበት ደረጃ መስፋትና መጠናከር እንዳለበት ነው ያሳሰቡት።

በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ ለመጣል የወጡ ረቂቅ ሕጎችም በጦርነቱ የተጎዳውንና ችግር ላይ የወደቀውን ሕዝብ የሚጎዱና ሰብዓዊ ቀውስ እንዲስፋፋ የሚያደርጉ መሆኑን መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።



የባልሲሊ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ምርምር ተቋም ዳይሬክተር አን ፊትዝ ጄራልድ

## ሕዝብና መንግሥት በቅንጅት በሠሩባቸው አካባቢዎች በሸኔ ላይ ድል መገኘቱን የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ሕዝቡ ተደራጅቶ ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በተሠራባቸው አባቢዎች በሸኔ ላይ ሰፊ ድል መገኘቱንና በተቃራኒው የሕዝብ ድጋፍ በቀዘቀዘባቸው አካባቢዎች ክፍተት መታየቱን ኦሮሚያ ክልል መንግሥት አስታወቀ።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ፣ የክልሉ መንግሥት ከመጋቢት 30 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ያካሄደውን የ3ኛ ሩብ ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ግምገማን አስመልክተው መግለጫ ሰጥተዋል። ኃላፊው በመግለጫቸው እንዳሉት የሸኔን አረመኔነት በመረዳት ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን በመቆም ቡድኑን ለማጥፋት በቆረጡ አካባቢዎች አንጸባራቂ ድሎች ተገኝተዋል።

የቡድኑን አደገኛነት ባለመረዳት ድጋፉ በተቀዛቀዘባቸው አካባቢዎች ክፍተት መታየቱንና በቀጣይ ሕዝቡን በማሳመንና በማንቀሳቀስ በሸኔ ላይ የሚወሰደው ርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል።

ምሥራቅ ሸዋ ፈንታሌ ቆርኬ አካባቢ በጽንፈኞች አማካኝነት ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ያስታወሱት አቶ ኃይሉ ጉዳቱን ባደረሱ ጽንፈኖች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የጋራ ኮሚቴ አቋቁመው እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ገለጻ ክልሉ በዘጠኝ ወራት ሥራ አፈጻጸም በፀረ ሠላም ኃይሎች ድርጊት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖም በልማቱ በኩል አበረታች ውጤቶችን ማስመዝገቡን ገልጸዋል።

ክልሉ የብልጽግና ጉዞ ዕቅዱን ለማሳካት በዕቅድ መመራት፣ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆን በሸኔና በጽንፈኞች የሚከሰተውን የሠላምና ፀጥታ ችግሮች በመመከት አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸው እንደጠንካራ ጎን አንስተዋል።

የሠላምና ፀጥታ ችግሮችን በፖለቲካዊ እርምጃዎች በመታገዝ እንዲፈቱ ከማድረግ አንጻር ሕዝብ ተደራጅቶ የአካባቢውን ሠላምና ልማት እንዲጠብቅ ማድረጉን አንስተዋል። ሠላምና ፀጥታ ችግሮችን በፖለቲካዊ እርምጃዎች በመታገዝ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች የተሻለ ድል ለማስመዝገብ ያደረጉት ጥረት አበረታች መሆኑን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በስንዴ ምርት ተሳትፎ አመርቂ ምርት እንደተገኘ ሁሉ የፀጥታ ችግሮችን በፖለቲካዊ እርምጃዎች ለመፍታት በሚደርጉ ሥራዎች እኩል አለማሳተፍና በተቀናጀ መልክ ተግባራዊ አለመደረጉ እንደደካማ ጎን ተወስደዋል። የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ገቢ አሰባሰብ ሂደት መንጠባጠቦች መታየታቸውን አያይዘው ገልጸዋል።

አቶ ኃይሉ በመግለጫቸው ክልሉ ጠንካራ ጎኖቹንና ደካማ ጎኖቹን መሠረት በማድረግ ቀጣይ ሦስት ወራት የሚሠሩ ሰባት ነጥቦች አብራርተዋል። በሕዝብ ተሳትፎ የጠላትን እንቅስቃሴ በማጋለጥ ጠላትን ማዳከም፣ ለዚህም ስኬት ጋቸና ሥርና (የሥርዓት ጋሻ) ሕዝብ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣ ሸኔ ባለበት ቦታ ሁሉ በትጥቅ የታገዘ ትግል ማካሄድ፣ ትኩረት የሚሰጥባቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በሌላም በኩል አርሶ አደሩ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ እንዲያዘጋጅና እንዲጠቀም ማድረግ፣ ለአረንጓዴ አሻራ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች ማከናወን በቀጣይ ወራት ከሚካሄዱ ሥራዎች ውስጥ እንደሚጠቀሱ ገልጸዋል። በቀሪ ጊዜያት ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅና አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል የክልሉ መንግሥት በትኩረት ለማከናወን ማቀዱን ጠቁመዋል።

የክልሉ መንግሥትም አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል እንቅፋት በሆኑ 10ሺህ በሚሆኑ የመንግሥት ሠራተኞችና አመራሮች ላይ እርምጃ መወሰዱንም ገልጸዋል።

# «ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን የሰላም ሂደት የማይተካ ሚና እየተጫወተች ነው»

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን የሰላምና መረጋጋት ሂደት መሳካት የማይተካ ሚና እየተጫወተች ነው ሲሉ በኢትዮጵያ የደቡብ ሱዳን አምባሳደር ጄምስ ፒቲአ ሞርጋን አስታወቁ። የአገራቱ ግንኙነት መጠናከር ጠቀሜታው ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ጭምር መሆኑን አምባሳደሩ ገልጸዋል።

ጄምስ ፒቲአ ሞርጋን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን የሰላምና መረጋጋት ሂደት መሳካት እያበረከተችው ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

የደቡብ ሱዳን መረጋጋት የኢትዮጵያም መረጋጋት ነው ከሚል እሳቤ የመነጨው ድጋፍ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና እንዲረጋጋ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህ የኢትዮጵያ አቋም ለደቡብ ሱዳናውያን ትልቅ ትርጉም አለው ብለዋል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የደቡብ ሱዳናውያን ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ የሚያደርጉት ጥረት የሚደነቅ ነው፤ ይህ ወንድማዊ አካሄዳቸውም ኢትዮጵያ ምንጊዜም ከደቡብ ሱዳን ጎን እንድትቆም የሚያደርጋት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን እ.አ.አ. በ2018 በአዲስ አበባ የተፈራረሙት ስምምነት የቀጣናውን ደህንነት ከማረጋገጥ አኳያ ጠቀሜታው የማይናቅ ነው ሲሉ ገልጸውታል።

በኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ የተመራው ልዑክ በደቡብ ሱዳን ጁባ ያደረገው ቆይታ ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ሂደት ያበረከተችውን አስተዋጽኦ ከፍ ያደረገ አጋጣሚ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተለያዩ ችግሮች በተከበበችው ምሥራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያና ደቡብ በጋራ ለመሥራት የሚያደርጉት ጥረት ቀጣናውን በማረጋጋት ሂደት ቀና ውጤት እንደሚያመጣ ይገመታል ብለዋል።

ኢትዮጵያና ሱዳንና በጋራ ጉዳዮቻቸው በተለይም በፖለቲካ፤ በሰላምና መረጋጋት በትብብር መሥራታቸው ከአገራቱ የኢኮኖሚያዊ ትስስር አልፈው ቀጣናቸውም እንዲረጋጋ ያደርጋሉ። ይህም የምሥራቅ አፍሪካ በተሻለ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲኖረው የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

የሁለቱ አገራት መንግሥታት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና



ጄምስ ፒቲአ ሞርጋን

ባህላዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ መስተጋብራቸው እንዲጎለብት ጠንክረው እየሠሩ ይገኛል። ደቡብ ሱዳን ከህዳሴ ግድብ ኤሌክትሪክ ለመጠቀም ፍላጎት አላት። ይህ እንዲሳካ የአገራቱ ግንኙነት መጠናከሩ መልካም አጋጣሚ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያና የደቡብ ሱዳን ግንኙነት ታሪካዊ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በቀጣይም ይህ ግንኙነታቸው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን ብሎም ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት ሂደት የምታደርገው አስተዋጽኦ ምስጋና አቅርበዋል።

ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳንም እ.አ.አ. በየካቲት 2017 በጸጥታ፣ ንግድና የድንበር አካባቢ ልማት ላይ በጋራ ለመስራት በጁባ ስምምነት ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

በተጨማሪ በመሠረተ ልማት ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻል ጋምቤላንና የተለያዩ የደቡብ ሱዳን ከተሞችን በአስፓልት መንገድ ለማገናኘት እንዲሁም ከዲማ ወደ ተለያዩ የደቡብ ሱዳን ከተሞች የአስፓልት መንገድ ለመዘርጋት ስምምነት አድርገዋል ብለዋል።

አገራቱ ሰፊ የድንበር ክልል የሚጋሩ በመሆናቸው በይበልጥ ግንኙነታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉበት ዕድል አለ፤ ይህም የቀጣናውን ልማት በማሳደግ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት በኢኮኖሚና በጸጥታ ጉዳዮች በጋራ እንዲሠሩ የማድረግ አቅም አለው ሲሉ ተናግረዋል።

የሁለቱ አገራት ከዚህ ባለፈ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የተሳሰረ ነው የሚሉት አምባሳደሩ፤ ደቡብ ሱዳናውያን ስለኢትዮጵያ ሲናገሩ ሁለት አገር ብንሆንም ወንድምና እህት የሆንን አንድ ሕዝቦች ነን የሚል ዕምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

በደቡብ ሱዳናውያን መካከል የነበረውን ችግር እንደሚቀርፍ ተስፋ የተጣለበትና በፕሬዚዳንት ሳልቫኪርና በምክትላቸው ሬክ ማቻር መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት እ.አ.አ. በ2018 የተደረሰውን የአገሪቷን ጦር በአንድ ዕዝ ስር የማድረግ ስምምነት የማስፈጸም ሂደት ነው።

# አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ በክልሉም ሆነ በፌዴራሉ መንግሥት ጉዳዩን በገለልተኛ አካል ለማጣራት ቀደም ተብሎ የታቀደና አቋም የተወሰደበት፤ በዚህም ወደ ተግባር ተገብቶ የጥናት ውጤቶች ይፋ እየተደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ በኩል የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን ባደረጉት ምርመራ በወጣው ሪፖርት መንግሥት የማይቀበላቸው ጉዳዮች በምርመራው ቢካተቱም የምርመራ ውጤቱን ግን መንግሥት እንደተቀበለው አውስተዋል።

በዚህ ደረጃ መንግሥት ግልፀኝነት፣ መልካም ፍቃድና ለተጠያቂነትም ዝግጁ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ለአንድ ወገን ብቻ በመወገን ሌላኛውን ደግሞ በመኮነን የወጣው ሪፖርት አግባብነት እንደሌለው አስረድተዋል።

ተቋማቱ ያወጡት ሪፖርት ፍትሃዊነትና ግልጸኝነት የሌለው፣ የተሠራበት አግባብ ይዘትና አላማው ከመነሻው ጀምሮ ትክክል አለመሆኑን አምባሳደሩ ገልፀው፣ በመንግሥት በኩል በሰብአዊ መብት ጥሰቶች ጉዳይ ላይ ገለልተኛ አጣሪ ቡድኖችን በማቋቋምና ምርመራ በማድረግ በአጥፊዎች ላይ እርምጃ የመውሰዱን አቅጣጫ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ሰብአዊ መብትን የመጠበቅና የመንከባከብ የመንግሥት አንዱ አላማ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚሠሩ ተግባራትን መንግሥት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አምባሳደር ዲና ተናግረዋል።

ከአንድ አካባቢ ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ወገኖች መረጃዎችና ሰነዶች ከመሰብሰባቸውም በላይ ይህን ጥናት አደረግን የሚሉ ተቋማት የተጠቀሙት ሰነዶችና መረጃዎችም ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መቃኘታቸው ሪፖርቱ ከወገንተኝነት ያልፀዳ መሆኑን ያመላክታል ብለዋል።

የአማራ ክልል አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች በጋራ ያወጡትን ሪፖርት እንደማይቀበለው እና በሪፖርቱም የቀረበው ክስና ውንጀላ የተቋማቱን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት የሚያሳብቅ መሆኑን መግለፁ ይታወሳል።

# ‹‹የእስካሁኑ ጥፋት ይብቃ፤

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ተቀዳሚ ሙፍቲው አገራዊ ምክክሩ ወደታች ወርዶ ተፈፃሚ እንዲሆን እንዲሁም አገር ወደ ሰላማዊ ሁኔታዋ እንድትመለስ ከመንግሥትና ከኅብረተሰቡ ብዙ ይጠበቃል ብለዋል።

ሕዝቡ ጥፋተኛን ለይቶ በማውጣትና የጥፋት መንገዶችን በመዝጋት የአገሪቱን ሰላም ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ኮሚሽኑም ከኢትዮጵያውያን ጋር በመማከር በጋራ ችግሮች የሚስተካከሉበትንና ወደ ሰላም የሚገቡበትን ዕድል መፍጠር እንደሚገባው ጠቁመዋል።

አገራዊ ምክክሩን ተግባራዊ ለማድረግ ጠበቅ ያለ መመሪያና ሕግ ሊኖር እንደሚገባ የጠቆሙት ሃጂ ዑመር፤ አገራዊ ምክክሩ በአገሪቱ የጠፋውን ሰላም ለመመለስና በዘላቂነት አብሮ ለመኖር ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

እንደ ተቀዳሚ ሙፍቲው ገለፃ፤ ከዚህ ቀደም በጦርነትና በሌሎችም ምክንያቶች የጠፋው ጥፋት ጠፍቷል፣ በደረሰው ውድመት የወደመው ወድሟል፣ የተፈናቀለው ተፈናቅሏል፣ አሁን ግን የጠፋው ጥፋት ይበቃል በማለት እርስ በእርስ መቋሰልን ትቶ ፊትን ወደ ሰላም ማዞር ይገባል።

እንደ ሃይማኖት አባትነቴ ሰላም እንዲሰፍን እንዲሁም መጋደልና መጫረስ እንዲበቃ እማጸናለሁ ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲው፤ አገራዊ ችግሮችን በንግግር በውይይት መፍታት እንደሚያሻም ጠቁመዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ንግግር፤ የሰው ልጅ ሰላም ምንጩ ፈጣሪውን መፍራት መቻሉ ነው፤ ፈጣሪውን መፍራት የቻለ ሰው ደግሞ የራሱን ሰላምና መብት አክብሮ የሌሎችን ሰዎችንም መብትና ሰላም ያስከብራል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከውይይት ማግስት የታዩ የአገልግሎት መሻሻሎች ሲሰፉም፣ ሲዘልቁም ይገባል!

ከ27 ዓመታት የጭቆናና አፈና ጉዞ በኋላ፤ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የፍትሃዊ ተጠቃሚነት አለመኖር፣ ከሥራ አጥነትና ሌሎችም ብልሹ አሠራሮች ምክንያት በሕዝባዊ እምቢተኝነት አዲስ ለውጥ በመጣ ማግስት፤ የዜጎችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መፍታት የለውጡ አመራር የቤት ሥራዎች ነበሩ፡፡ የለውጡ ኃይልም እነዚህን የመፍቻ ስልት ቀይሶና ይሄንኑ ለማድረግ የሚያስችሉትን አቅጣጫ አስቀምጦ ወደሥራ ገብቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የሕዝቦችን የመልካም አስተዳደር ችግር መፍታት ሲሆን፤ ይሄም ብቁ፣ ገለልተኛና ነፃ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግሥትን የመፈጸም ብቃት ማጎልበትና የአገልግሎት አሠጣጥን ማቀላጠፍና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን ርካታ ማሳደግን ታላሚ ያደረገ ነበር፡፡

ይሄን እውን ለማድረግም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በርካታ ሥራዎች የተሠሩ ቢሆንም፤ ሂደቱ ግን በተፈለገው ልክ የተጓዘ ሳይሆን በብዙ ፈተናዎች የታጀበ፣ ይልቁንም የዜጎችን የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት ችግሮችን ከመፍታት በላይ ሰላምና ደህንነታቸውን ማስጠበቅ ትልቁ የቤት ሥራ ሆኖ ከርሟል፡፡ ይህ ደግሞ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በይደር ሲንከባለሉ እንዲዘልቁ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ከዕለት ዕለት የተንዛዛና ለብልሹ አሠራር በር የከፈተ እንዲሆን አደረገ፡፡ እንደ አገር ከተጋረጠው የሕልውና አደጋ ባልተናነሰ ሌላ አደጋ ተደቀነ ችግር እስከመሆንም ደረሰ፡፡

ከለውጥ ማግስት ቃል የተገባው የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥያቄ ሳይመለስ በዚህ መልኩ ቢቆይም፤ የለውጥ ሂደቱ በምርጫ ታግዞ እንደ አገር በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት እውን መሆን ስለነበረበት ስድስተኛው አገራዊ ምርጫ በፈተናዎች ውስጥም ተሁኖ እንዲካሄድ የግድ ሆነ፡፡ ለዚህ ምርጫ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተወዳደሩ ሲሆን፤ ሕዝብ የቀረበለትን የሃሳብ ብፌ ተመልክቶ ይሆነኛል ያለውን መርጦ ለአምስት ዓመታት መንግሥቱ አድርጎ ሾሟል፡፡ በዚህም የለውጥ ሂደቱን በበላይነት ይዘው ሲጓዙ የነበሩትን ኃይሎችን ያቀፈውን ብልጽግናን በመምረጥ ያደሩ ጥያቄዎቹን ይፈታለት ዘንድ መጠበቅ ያዘ፡፡

ብልጽግናም በምረጡኝ ቅስቀሳው ቃል ከገባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የሕዝብን የመልካም አስተዳደር ችግርና የአገልግሎት አሰጣጥ ትብታብን የመፍታት አንዱ ሲሆን፤ ለዚህም ብቁ፣ ገለልተኛና ነፃ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት መገንባት፤ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ሥራ አመራር ሥርዓት ማሻሻል፤ የሕዝብ ሠራተኞችን እሴት መገንባትና ሥነምግባርን ማሻሻል፤ ውጤታማ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፤ በሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት በአገራዊው የልማት ጉዞ ጉልህ ሚና መጫወትን የመሳሰሉ የሕዝብ አገልግሎቱን የሚያሳልጡና የመልካም አስተዳደር ችግሩን ይፈታሉ የተባለላቸው ብልጽግና ፓርቲ እንደ መንግሥት የቀጣይ አስር ዓመታት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎቹ ናቸው በሚል ነበር ያቀረበው፡፡

ሕዝብም በዚህና መሰል ቃሎች እማኝነት የአምስት ዓመት ኮንትራቱን ሰጥቶ ከምርጫ ማግስት እንደ ቀደመው ሁሉ ችግሮቹ እንዲፈቱለት እየተጠባበቀ ባለበት ሂደት በድጋሚ ከችግሩ የባሰ ችግር የአገር ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ወደቀ፡፡ እናም ለጊዜውም ቢሆን ሁሉም ፊቱን አገር ወደማዳን አዞረ፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ ችግሩ የበለጠ እንዲጎለብት፤ እንደ አገር የሁሉም አካባቢ ጥያቄ እንዲሆን አደረገ፡፡ ብልጽግናም አገርን ከማዳን ተልዕኮው መለስ ሲል፤ ጠቅላላ ጉባኤውን በማካሄድ የችግሮቹን ስፋትና ግዝፈት በመገንዘብ ዐብይ አጀንዳውም፤ ዋና ትኩረቱም አድርጎ ጉባኤውን አጠናቀቀ፡፡ ችግሩን የበለጠ ለመገንዘብም ወደ ሕዝብ ደርሶ መወያየትን እንደ አንድ አቅጣጫ አስቀምጦ በሥራ አስፈጻሚና በማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሕዝባዊ መድረኮች ተካሄዱ፡፡

እነዚህ መድረኮችም ያለ ልዩነት ሁሉም ቦታዎች የሕዝብ ብሶቶች የተስተጋባባቸው ነበሩ፡፡ ሰላምና ፀጥታ፣ መልካም አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ሙስና፣ ወዘተ. የሚሉ ቃላት በተመሳሳይ ብሶትና ሮሮ ተደመጡ፡፡ ይህ ደግሞ ብልጽግና እንደ መንግሥት ቆም ብሎ ራሱን እንዲያይ፣ እንዲፈትሽና የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ግድ ያለው ነበር፡፡ እናም የእርምት እርምጃዎችን ከአመራሩ ጀምሮ ወደታችኛው ባለሙያ እስኪወርድ አለፍ አለፍ ብሎ መነቃቀል ያዘ፡፡ ይሄን ተከትሎ የሕዝብ ምሬት ይደመጥባቸው የነበሩ ቀበሌዎችና ወረዳዎች የተወሰኑ መሻሻሎች ታዩባቸው፡፡ ተገልጋዮች ከግልምጫና ወከባ እንዲሁም እጅ እጃቸው እየታየ ከሚያገኙት አገልግሎት እፎይ ያሉባቸው ቀበሌዎችና ወረዳዎች መፈጠራቸውም ተሰማ፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ለውጥና መሻሻል በሁሉም አካባቢዎች፣ በሁሉም ቀበሌዎችና ወረዳዎች መድረስ አለመቻሉም ይነገራል፡፡ ይህ ደግሞ የጥቂት መልካም ጅምር ያሳዩ አካባቢዎችን ሥራ ጭምር ጥላሸት የሚቀባ የማይለወጥ መጥፎ አመል ውጤት ነው፡፡ ሕዝብ ደግሞ በሁሉም ቦታና ሥፍራ ያለ ልዩነት ሊስተናገድ፤ ተገቢውን የመንግሥት አገልግሎት በተገቢው ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ ሊያገኝ የግድ ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ ከውይይት ማግስት በተወሰኑ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የታዩ የአገልግሎት መሻሻሎችን ማስፋት፤ እንዲሁም መሻሻል የታየባቸውም ጅምራቸውን ዘላቂ እንዲያደርጉ ማስቻል ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# ‹‹ብሔራዊ ደወሉ ተደውሏል...!!››

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበባ (ለንደን)**

እንደምን አላችሁልኝ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወዳጆቼ፤ በቅርቡ በአገራችን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀው የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች ምርጫ ተጠናቆ በቀጣይ ወራቶች ሥራቸውን እንደሚጀምሩ በጉጉት እየተጠባበቅን ነው። ባለፉት አስርት ዓመታት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮቻችን ቢቻል ሁሉንም ካልተቻለም ዋና ዋና የምንላቸውን ሰንኮፎች ነቅለን ጥለን አርቀን ለመቅበር ብሔራዊ ደወሉን በእርግጥ ደውለናል።

አገራዊ ምክክሩ ሁሉንም አካታች በሆነ መልኩ ለመፍታትና ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር ኮሚሽኑ ከሚኖረው ከፍተኛ አገራዊ ኃላፊነት አኳያ ለኢትዮጵያ በሚበጅ ሁኔታ የሌሎች አገራትን ተሞክሮ በመውሰድ አዳዲስ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ውጤታማ ሥራዎችን ይሠራል ተብሎ ተስፋ ጥለንበታል።

እንደዚህ ዓይነት ግዙፍ አጀንዳ ለኮሚሽኑ ወይንም ለመንግሥት አካላት ብቻ የሚተው ሸክም ሳይሆን ሕዝብን እንወክላለን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ኃላፊዎች አገራዊ ምክክሩ በአንዳንድ ልግመኛ ምሁራኖችና ፅንፈኛ ፖለቲከኞች እንዳይጠለፍ መጠንቀቅ አለባቸው። በተለይ የሰመረ ውጤት እንዳያመጣ ሊያደናቅፉ የሚያስቡትን ሴረኞች ማጋለጥና ታሪካዊ ኃላፊነትን ወስዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ማስጠበቅ ያገባኛል የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግዴታ ነው።

እዚህጋ «አንድነት» ስንል ብሔራዊ የዜግነት ግዴታ ማለታችን ነው። ያለአንድነት አገራዊ ምክክሩ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ያለ አንድነት ሉአላዊነት ጤና ልማት ትምህርት የተለያዩ አጀንዳዎችን ይዘን ብንመጣም ሁሉም ትርጉም የለላቸው፤ የመወያያ እርዕሶች ብቻ ሆነው ነው የሚቀሩት።

በቅድሚያ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትቀጥል የምንስማማበት የአንድነት አጀንዳችን መሆን አለበት። በዚህ አጀንዳ የምንስማማ ከሆነ ያሉንን የልዩነት በሰከነና አስተማማኝ በሆነ ብልሀት መፍታት እንችላለን። ለአገራዊ ምክክር ዋስትና የሚሆነውም ይኸው አብሮነታችን ነው።

በጋራም የምንስማማበት ኢትዮጵያም እንደ አገር

> አገራዊ ምክክሩን በፅንፈኛ ፖለቲከኞች የምናጨናግፈው ከሆነና ሕብረት ካጣን የመተማመንና የመረዳዳት እሴት ካልገባን ለወገን ተቆርቋሪ መስለን ለጠላት ካደርን፣ ዘረኛ ፖሊሲ ገንብተን ፅንፈኝነትን ከመረጥን የኢትዮጵያ ክብር መሆን ቀርቶ ማፈሪያ ሆነን የልመና ኮሮጆችንን ይዘን ወደ ሌላ ዓለም በመሰደድ በየእስር ቤቱ ታዛ ወድቀን የመንግሥት ያለህ እያልን ማልቀሳችን የማይቀር ነው

ልትፀና የምትችለው በጠንካራ ሕዝባዊ አንድነት በመሆኑ ለችግሮቻችን ሁሉ ስኬታማና አስተማማኝ መፍትሔ ልንሰጥ የምንችለው በአንድነት ለአንድ አገር ስንቆም ነው። ዋናው አገራዊ ውይይት ጠቀሜታው ይኸው ነው።

የሁሉም ብሔረሰቦች እኩልነት እንዲረጋገጥና አንድነታቸው እንዳይፈርስ በባህል፣ በታሪክ፣ በሃይማናት፣ በምጣኔ ሀብት የተቆራኘን በመሆናችን ኢትዮጵያዊነት በታሪክ የተገነባ መሆኑን መተማመን ያስፈልጋል። ዛሬ H.R. 6600 እያለች የምትመፃደቀዋ አሜሪካም ሆነች ሌላው ዓለም የእኛን የእርስ በእርስ ጦርነት ከርሀብና ከበሽታ ከኋላ ቀርነት በአጠቃላይ ከተረጂነት መንፈስ የምንላቀቅበትንና እራሳችንን የምንችልበትን፣ አካሄድ አይፈልጉትም።

የእኛ በአንድነት መቆምና ብዙ የችግር ዘርፎችን ድል ማድረጋችን አገራዊ ምክክር መጀመራችን የምሥራቅ አፍሪካ ኃያልነታችንን እንደሚያበስር ስለሚረዱ ቅን ያሰቡ መስለው አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች የሚል ታፔላ እየለጠፉ እርስ በእርስ ጣት እንድንጠቋቆም ያደርጉናል።

ከዚያም ባለፈ ከተረጂነት መንፈስ እንዳንላቀቅ በዘር ፖለቲካ እንድንታመስ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ጠላቶች ደግፈው የተከፈተብንን የህልውና አደጋ በተባበረ ክንዳችን እንዳንከላከል በብድርና በእርዳታ ማዕቀብ የማስፈራሪያ አንቀፅና ሕግ እያረቀቁ ሕዝባችንን የስነ ልቦናና የፕሮፖጋንዳ ሰለባ ያደርጉብናል። ከአሁን በኋላ ግን ይምረረንም ይጣፍጠንም በታሪክ ፊት ቆመን አንድ እውነት እንመሰክራለን።

ድሮም ያልሆነብንን ዛሬም ሆነ ወደፊት እንዲሆንብን አንፈቅድም፤ በቀጣይም ነፃና ሉአላዊት ኢትዮጵያ አገራችን በውጭ ሞግዚት ልተመራ የምትችልበት ምንም ዓይነት የታሪክ ቆሻሻ ምልክት የለብንም። አገራዊ ምክክሩ ደግሞ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት በጋራ ስምምነት በአንድነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው።

አገራዊ ምክክሩን በፅንፈኛ ፖለቲከኞች የምናጨናግፈው ከሆነና ሕብረት ካጣን የመተማመንና የመረዳዳት እሴት ካልገባን ለወገን ተቆርቋሪ መስለን ለጠላት ካደርን፣ ዘረኛ ፖሊሲ ገንብተን ፅንፈኝነትን ከመረጥን የኢትዮጵያ ክብር መሆን ቀርቶ ማፈሪያ ሆነን የልመና ኮሮጆችንን ይዘን ወደ ሌላ ዓለም በመሰደድ በየእስር ቤቱ ታዛ ወድቀን የመንግሥት ያለህ እያልን ማልቀሳችን የማይቀር ነው።

ይህ ደግሞ ትንቢት ሳይሆን እውነት ሆኖ በዓይናችን ያየነው ስለሆነ እንደ አገር የማንቀጥልበትም ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አገራዊ ምክክሩ በሴረኞች እንዳይጠለፍ ተጠንቅቀን በብልሀትና በፖለቲካ ብቃት ይዘን ብሔራዊ ማንነት ላይ ደርሰን አንድነታችንን ማስቀጠል ይኖርብናል።

ሌላ ሌላውን ቀስ እያልን በሒደት የምንሠራው ቢሆንም ለአገርና ለሕዝብ የማይበጁ አመራሮችን ከመጨረሻው የስልጣን እርብርብ እስከ ከፍተኛው የስልጣን ደረጃ ያሉ ሰዎችን ከተቀመጡበት ወንበር አሽቀንጥረን ጥለን ሊሠሩ በሚችሉት በአዳዲስ የአንድነት ራዕይ ባላቸው የመደመር ጭንቅላቶች መተካት ይኖርብናል። ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ፤ በሌላ ዝግጅት እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን።

*ሰላም!*

# ነፃ ሃሳብ

# ኢትዮጵያ - ለእስልምና ሃይማኖት ያላት አበርክቶ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ኢትዮጵያ እንደ አገር፣ ኢትዮጵያውያን ደግሞ እንደሕዝብ ከሌሎች የዓለም አገራትና ሕዝቦች ለየት የሚያደርጓቸው በርካታ ነገሮች መጥቀስ ይቻላል። አገራችን ኢትዮጵያ የራሳቸው ፊደልና የዘመን መቁጠሪያ ካላቸው ጥቂት የዓለማችን አገራት አንዷ ከመሆኗ በተጨማሪ በቅዱስ መጽሐፍት በተደጋጋሚ የተጠቀሰች፣ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቅርሶችና ብርቅዬ እንስሳቶች ባለቤት፣ ከሰማንያ በላይ ቋንቋዎች የሚነገሩባት፣ የሃይማኖት እኩልነትን ከማንም ቀድማ ያወጀችና ሃይማኖቶቹም ለዘመናት ተከባብረው የኖሩባት፣ እሷን ብለው ለመጡ መጠለያ እንደምትሆን ሁሉ ሊያጠቋት ለመጡ የውጭ ጠላቶች መቀበሪያ የሆነችና የጀግኖች አትሌቶች መፍለቂያ አገር መሆኗን ሁሉም ይመሰክርላታል።

በተጨማሪም ከምንም ነገር በላይ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩ ሃይማኖተኞች፣ እንግዳ ተቀባዮች፣ ሰው አክባሪዎችና በተደጋጋሚ ጊዜያት ከውጭ ጠላቶች የሚሰነዘሩባቸውን ጥቃቶች በመመከት ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩ እንዲሁም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በጭቆና ውስጥ ለነበሩ ሕዝቦችም የነጻነት ተምሳሌት መሆን የቻሉ ሕዝቦች ያላት ድንቅ አገር ናት።

ከላይ ከተዘረዘሩት ማሳያዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ለየት የሚያደርጓቸው በርካታ ነገሮች መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያ ለእስልምና ኃይማኖት ያበረከተቻቸውን አስተዋጽዖዎችና ከዓረቡ ዓለም ሙስሊም አገራት ለየት የሚያደርጓትን ነገሮች ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ማስተያየት ነው።

ሼኽ ዑመር ሼኽ በሽር በአረብኛ ቋንቋ በጻፉትና ሼኽ አብደላህ መሐመድ ዓሊ ወደ አማርኛ በተረጎሙት መጽሐፍ እንደተገለጸው፤ ነብዩ መሐመድ ገና ሕጻን እያሉ እናታቸው በሞት ስላጡ እሳቸውን ያጠባች ሐበሻዊት (ኢትዮጵያዊት) ሴት መሆኗ፣ እስልምናን በመቀበላቸው ምክንያት አገራቸውን ለቀው እንዲሄዱ የተገደዱትን የነብዩ መሐመድ ቤተሰቦችና ባልደረቦች (ሶሃባዎች) ማስጠለላችን፣ አረቦች እንዳይተናኮሉን ነብዩ መሐመድ ማዘዛቸው፣ የሐበሻ ሰዎች ጥሩነት በቁርዓን ውስጥ መገለጹ፣ የተሻለ ፍትህ እንዳለን በነብዩ መሐመድ መመስከሩ፣ ነብዩ መሐመድን ከዑሙ ሀቢባ ጋር ያጋባንና በጋብቻ ወቅት የሚከፈለው ክፍያ (መኽር) የከፈልን በመሆናችን፣ የነብዩ ቤተሰቦችና ታላላቅ ሰሃባዎች (ባልደረቦች) ለብዙ ዓመታት በአገራችን መኖራቸው፣ በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያው አዛን (ለሶላት የሚደረግ ጥሪ) አድራጊ የቢላል አል-ሐበሻ ወገን መሆናችንና ሌሎችም ነገሮች ሙስሊም አራትን ጨምሮ ከዓለም አገራት ለየት ያደርጉናል።

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ዓመታት ነብዩ መሐመድ እስልምናን ማስተማር በጀመሩበት ወቅት የራሳቸው የመካ ሕዝቦች በከፍተኛ ሁኔታ ያሰቃዩአቸው ስለነበር መጠጊያ ያልነበራቸው ተከታዮቻቸው “ወደ ሐበሻ ምድር ሂዱ፤ እዛም እርሱ ዘንድ ማንም የማይበድል የሆነ መንግሥት ታገኛላችሁ፤ ፈረጃ (መፍትሄ) እስኪገኝ ድረስም እዛ ቆዩ” በማለት ወደ ሐበሻ ምድር ላኳቸው።

የስደተኛ ቡድኑ አስራ አንድ ወንዶች እና አራት ሴቶችን ይዞ የነበረ ሲሆን፤ ከእነሱም ነብዩ መሐመድ ከሞቱ በኋላ ሶስተኛው የሙስሊሙ ዓለም መሪ የሆኑት ዑስማን ኢብኑ አፋን እና ባለቤታቸው፣ እንዲሁም የነብዩ መሐመድ ልጅ የሆነችው ሩቂያ ይገኙበት ነበር። ይህ በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያው ስደት ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፤ ቀጥሎም ከ82 በላይ ሙስሊም ስደተኞች በጃዕፈር ኢብኑ አቡ-ጣሊብ እየተመሩ ወደ ሐበሻ ምድር ዘልቀዋል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ የበድር ጦርነት በተከሰተና ቁረይሾች በሙስሊሞች በተሸነፉ ጊዜ በቀላቸውን ወደ ሐበሻ በተሰደዱት ላይ ሊወጡ አሰቡ። ከውድ ስጦታዎች ጋር ሁለት ሰዎች ወደ ንጉሥ ነጃሺ ተላኩ። ንጉሥ ነጃሺም በውድ ስጦታዎች ሳይታለሉ የሁለቱም ወገን ሃሳብ ካደመጡ በኋላ ስደተኞችን ከቁረይሾች አስጥለው “በምድሬ ላይ ተረጋግታችሁ ኑሩ፤ እናንተን በክፉ የሚያይ ብርቱ ቅጣት ይጠብቀዋል” በማለት በሰላም እንዲኖሩ ፈቀዱላቸው።

ንጉሡ ወደ ቁረይሽ ተወካዮች ዞረው “ተራራን የሚያህል ወርቅ ብትሰጡኝ እንኳን እነዚህን ስደተኞች አሳልፌ አልሰጣችሁም” አሏቸው። ስደተኛ ሙስሊሞችን ለመበቀል የመጡት የቁረይሽ ሰዎችም የከሰሩ ሆነው ወደ አገራቸው ተመለሱ። ስደተኞቹ ደግሞ በንጉሥ ነጃሺና ማንም በማይበደልባት አገራቸው በጥሩ እንክብካቤ ነብዩ መሐመድ ወደ መዲና እስከተሰደዱበትና ጠላቶቻቸውን እስካሸነፉበት ጊዜ ድረስ በሰላም ቆዩ።

አንጋፋው የታሪክ ተመራማሪ አደም ካሚል (ረዳት ፕሮፌሰር) እንደተናገሩት በወቅቱ ንጉሥ ነጃሺ ስደተኞቹን አሳልፈው ቢሰጡ ኖሮ የሰዎቹ ዕጣ ፈንታ መሞት ነበር፤ የእስልምና መሠረትም ይጠፋ ነበር። በወቅቱ መካ ውስጥ ወደ ሐበሻ የመጡ ስደተኞችን በስቅላት ለመቅጣት ገመድ ተንጠልጥሎ ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያ ለእስልምና ይህን ከባድ ውለታ ባትውል ኖሮ እስልምና አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ላናገኘው እንችል ነበር፤ ሲሉ ነው ረዳት ፕሮፌሰር አደም የሚያስረዱት።

በወቅቱ መካ ውስጥ እስልምናን መቀበል ያሳስር፣ ያስደበድብና ያስገድል ነበር፤ ቁርዓን ማንበብም ያስፈነክት ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያንና ንጉሳቸው የክርስትና እምነት ተከታዮች ቢሆኑም፤ ፍትሐዊና ስልጡን በመሆኗቸው በገዛ አገራቸው በእምነታቸው ምክንያት እንዲሰደዱ የተደረጉ ሙስሊም ስደተኞችን ከመቀበልና ከመንከባከብ አላገዳቸውም። ስደተኞቹ በቤተመንግሥት በንጉሡና ቀሳውስት ፊት በነጻነት ቅዱስ ቁርዓን ማንበባቸው በበርካታ ኢስላማዊ መጽሐፍት ተጽፎ ይገኛል።

አላህ (ሱ.ወ) ሐበሻን አስመልክቶ በቅዱስ ቁርዓን ሱረቱል ማኢዳ፥82 እንዲህ ብሏል፡- “...በውስጣቸው የተለያዩ ቄሶችና መነኮሳት ያሉ ሲሆን እነርሱም የማይኮሩና ሐቅ በመጣ ጊዜ የሚቀበሉ በመሆናቸው ነው”።

በወቅቱ ነብዩ መሐመድ ቤተሰቦቻቸውና ተከታዮቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲልኩ በአካባቢያቸው በብዙ ነገሮች የሚቀርቧቸው አገራት ወይም ነገሥታት ስላልነበሩ አይደለም ሐበሻን የመረጡት። በወቅቱ ዓለም ላይ ካሉ አገራት በተለየ ሁኔታ የሐበሻ ምድር ማንም የማይበደልባትና ፍትሐዊ መሪ ያላት እንዲሁም ሕዝቦቿና መሪዋ ክርስቲያኖች ቢሆኑም ለእምነት ነጻነትና ለሃይማኖት እኩልነት እውቅና የሚሰጡ ስልጡን ሕዝቦች በመሆናቸው እንጂ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንኳን ተግባራዊ ማድረግ ያልቻላቸውን ከእምነት ነጻነት፣ ከሃይማኖት እኩልነት፣ ከፖለቲካ ጥገኝነት፣ ከሰብዓዊ መብት ማስከበር፣ ስደተኞችን ከመቀበልና ከመንከባከብ፣ ሙስናን ከመዋጋት ጋር በተያያዘ የሚወጡ ዓለም አቀፍ ሕጎች ኢትዮጵያ ከዛሬ አንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት በንጉሧ አል-ነጃሺ አማካኝነት ተግባራዊ አድርጋቸዋለች።

በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ነገር የሙስሊም ስደተኞቹ መነሻ አገር የሆነችውና በሸሪዓ (ኢስላማዊ ሕግ) እንደምትተዳደር የሚነገርላት ሳውዲ አረቢያ፤ ዛሬ ላይ ለሥራ ብለው የሄዱ ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ኢትዮጵያ ጠል ከሆኑ ቡድኖች ጋር ተባብራ ከአገሯ እያስወጣች መሆኗ ነው። በዚህም የሳዑዲ ዓረቢያ መንግሥት የኢትዮጵያን ውለታ መመለስ አልቻለም፤ በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከአንድ ሺህ 400 ዓመት በፊት እንደነበረው የሐበሻው ንጉሥ ወደ አገሩ የገቡ ስደተኞች መንከባከብ ባይችል እንኳን በአገሩ በነጻነት እንዲኖሩ ማድረግ አልቻለም።

ሳውዲ ዓረቢያ እሷን ብለው የሄዱ ኢትዮጵያውያንን የምታንገላታውና ከአገሯ የምታስወጣው ኢትዮጵያ ለእስልምና የዋለችው ውለታ ወይም ነብዩ መሐመድ ስለኢትዮጵያ (ሐበሻ) የተናገሩትን ሳታውቀው ቀርታ አይደለም። ከሃይማኖት ይልቅ ፖለቲካ ስለምታስቀድም እንጂ!

ወደ ዋናው ጉዳዬ ልመለስና፣ ኢትዮጵያ ሙስሊም ስደተኞችን በመቀበሏ ብቻ አይደለም ከሌሎች የዓለማችን አገራት የምትለየው። ነብዩ መሐመድ ገና ሕጻን እያሉ ወላጅ እናታቸው በሞት ባጡበት ጊዜ ጡቷን አጥብታ ያሳደገች ሐበሻዊት ሴት ናት። በረካ አል-ሐበሺይ (ዑሙ አይመን) ትባላለች፣... ነብዩ መሐመድን ተንከባክባና ጡቷን አጥብታ ወደ አያታቸው አብዱልሙጠሊብ ዘንድ አድርሳለች።

በእስልምና ሕግ መሠረት የጋራ ጡት የጠቡ ማናቸውም ልጆች ወንድማማቾች/እህትማማቾች ናቸው። በዚህም መሠረት በረካ አል-ሐበሺይ ከነብዩ መሐመድ ቤተሰቦች ጋር በመቀላቀሏ ሐበሾች የሆኑት አባቷ፣ እናቷ፣ ወንድሟ፣ እህቷና ሌሎችም ቤተሰቦቿ ሁሉ ከነብዩ መሐመድ ጋር ተቀላቅለዋል ማለት ነው።

ነብዩ መሐመድ ካደጉ በኋላ ለበረካ ክብር ሲሉ ጋቢያቸውን መሬት አንጥፈው እንድትቀመጥበት ማድረጋቸው በበርካታ መጽሐፍት ተጽፎ ይገኛል። ይህም ከእርሷ ጋር የመጡትን ሁሉ ክብር ያጎናጸፈ ነበር። ነብዩ መሐመድ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ በረካ የጀነት (የገነት) መሆኗን አብስረዋታል።

ቡሰይሪ የተባሉ ዓሊም (ምሁር) “ሀምዚያ” በተባለው የግጥም ሥራቸው ላይ በረካ ነብዩ መሐመድን ጡት ያጠባች እንደሆነች ገልጸው፤ ክብሯም “የሰማይ ያህል የሰፋ ነው” ሲሉ ገልጸዋታል። ነብዩ መሐመድም፣ ከሌሎች አገራት በተለየ መልኩ ዓረቦች ሐበሻን እንዳይተናኮሉ “ሐበሾችን ሳይነኳችሁ አትንኳቸው!” በማለት ደንግገዋል።

ነገር ግን አሁን እየሆነ ያለው በተቃራኒው ነው። የነብዩ መሐመድን ትዕዛዝ በመተላለፍና የኢትዮጵያን ውለታ ከቁብ ሳይቆጥሩ ኢትዮጵያን እያስጨነቁ ካሉ አገራት አንዷ እስላማዊ አገር ነኝ የምትለዋ ግብጽ (ምስር) ነች። ግብጽ ኢትዮጵያውያን ትልቁ ሀብታቸው በሆነው የአባይ ወንዝ እየገነቡት ያለውን ታላቁን የህዳሴ ግድብን በመቃወም ኢትዮጵያ ላይ ዘርፈ ብዙ ጫና እንዲፈጠር ስትወተውት ቆይታለች፤ እየወተወተችም ትገኛለች።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሙፍቲህ ሐጂ ዑመር እንድሪስ ይህን ከእስልምና አስተምህሮ ያፈነገጠው የግብጽን አቋም ሲተቹና የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀምን በተመለከተ ሲያብራሩ፤ ሸሪዓው የሚለው የላይኛው የምንጩ ባለቤት ተጠቅሞ ሲያበቃ ለታችኛው ይልቀቅለት ነው፤ ይህ የግብጽ ዑለሞችም ያውቁታል ብለዋል።

“ከዚህ በተረፈ የግብጽ ወንድሞች በብርሃን ሲኖሩ የኢትዮጵያ ወንድሞች በጨለማ ይኑሩ የሚል ሃይማኖታዊም ሆነ ሌላም ሕግ አይኖርም። እናንተም በሙብራት እንደምትኖሩት እኛም በሙብራት እንኑር ነው ያልነው፤ ይህ ሸሪዓችን ያወድሰዋል እንጂ አያወግዘውም” ሲሉም ለግብጾች ጠንከር ያለ መልዕክት አስተላልፈውላቸዋል። እስልምናን እና ነቢዩ መሐመድን በመቀበል ብሎም እስልምናን በመርዳት እኛ ሐበሾች እንደምንቀድም፤ እንዲሁም ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያን ወንድሞቻችንም ነቢዩ መሐመድን ረዱ እንጂ አልወጉም ሲሉ ግብጻውያንን ሞግተዋል።

ሌላው ሐበሻን ከዓለም አገራት ለየት ከሚያደርጓት ነገሮች አንዱና ትልቁ የሐበሻ ሰዎች ጥሩነት በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ መገለጹ ነው። ሱለይማነል ጀመል ሀዚም የተባሉ ሰው፣ ኢብኑ አባስ አወሩት ብለው እንደገለጹት “እነዚያ እኛ ነሳራዎች (ክርስቲያኖች) ነን ያሉት ወደ ሙዕሚኖች (ሙስሊሞች) የቀረቡና የተወደዱ ሆነው በርግጥ ታገኛቸዋለህ” (ቁርዓን ሱረቱል ማኢዳ፥82) የሚለው የአላህ ንግግር ለሐበሾች እንደሆነ መስክረዋል።

ነብዩ መሐመድን ዑሙ ሀቢባ ከምትባለው ባለቤታቸው ጋር ያጋባንና በጋብቻ ወቅት ለሴቷ የሚሰጥ ገንዘብ (መኽር) የከፈልን መሆናችንም ለየት ያደርገናል። ነብዩ መሐመድ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ከመካ ወደ መዲና ከተሰደዱ በስድስተኛ ዓመት ወደ ነጃሺ አንድ ደብዳቤ ላኩ። በደብዳቤው ውስጥ ዑሙ ሀቢባ ቢንት አቡ ሱፍያን የተባለች ሴት ከባሏ ጋር ወደ ሐበሻ ተሰዳ ሳለ ባሏ በስደት ላይ በመሞቱ ነብዩ ሊያገቧት እንደፈለጉ የሚገልጸው መልእክት ይገኝበታል። ነብዩ መሐመድን በመወከል ለዑሙ ሀቢባ ከነጃሺ የተሰጠው መኽር 400 ዲናር ሲሆን በነብዩ ወገን ሆኖ ለጋብቻው (ኒካህ) ስኬታማነት ትልቁን ሚና የተጫወቱት የሐበሻው ንጉስ ነጃሺ ናቸው።

ሌላው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም በየሄደበት ሁሉ በጣም ከሚደሰትባቸውና ከኮራባቸው ነገሮች አንዱ በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያው አዛን አድራጊ (ለሶላት ተጣሪ) ቢላል ኢብኑ ረባህ (ቢላል አል-ሐበሻ) ኢትዮጵያዊ መሆኑ ነው። ቢላል ከነብዩ ታማኝ ባልደረቦች አንዱና ዋነኛው የነበረ ሲሆን እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት ከጠላቶች ቅጣትን ከመቀበሉ ባሻገር በቅጣቱ ሰዓት ባሳየው ታላቅ ጽናት የተነሳ “ወደ አላህ ተጣሪ” በሚል ከአላህ ሙግስናን አግኝቷል። በቅዱስ ቁርዓንም “ያ እርሱ ወደ አላህ ከሚጣራው የበለጠ ድምጹ ያማረ ማን ነው?” ተብሎ ተጠቅሷል።

በበርካታ እስላማዊ መጽሐፍት እንደተገለጸው ነብዩ መሐመድ ከአላህ ጋር ለመገናኘት ከጅብሪል (ገብርኤል) ጋር በመሆን ወደ ላይ (ሚዕራጅ) በወጡ ጊዜ በሐበሻ ምድር ብርሃናቸው እንደ ክዋክብት የሆኑ ሰዎች ተመለከቱ። ለጅብሪልም “እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?” ብለው ጠየቁት። “እነዚህማ ከዑመትህ ውስጥ የሆኑ ሐበሾች ናቸው!” ብሎ መለሰላቸው። ነብዩም “ጌታዬ ሆይ! እርዳቸው!” ብለው ዱዓ (ጸሎት) አደረጉ።

የነብዩ መሐመድ ልጅ ሩቂያ፣ በጣም የሚወዷቸውና የቅርብ አማካሪያቸው የሆኑት እንዲሁም ለእርሳቸው ያላቸው ከበሬታ የላቀና የሁለት ልጆቻቸው ባለቤት ዑስማን፣ የአላህ ካዝና በእርሱ እጅ ያለ የሚመስለው ሀብታሙ አብዱራህማን፣ ነብዩን በመልክ የሚመሳሰሉትና የአጎታቸው ልጅ የሆኑት ጃዕፈር፣ የዑለማዎች ኮከብ ተብለው የሚታወቁት ታላቁ አብደላህ ኢብኑ መስዑድ እና ሌሎችም የነብዩ መሐመድ ባልደረቦች ይህቹን አገር መርገጣቸው እንዲሁም ከእነርሱ በክብር ያልተናነሱ ታላላቅ የነብዩ መሐመድ ባልደረቦች በሐበሻ ምድር በሞት መቅረታቸው ዓለም ላይ ካሉ አገራት ሁሉ ኢትዮጵያን ለየት ያደርጋታል።

በተጨማሪም ስለ ሐበሻ ሰዎች የተጠቀሱ የቁርዓን አንቀጾችና ስለ ሐበሻ በነብዩ መሐመድ የተደረጉ ንግግሮች (ሐዲሶች) መኖራቸው፤ ንጉሥ ነጃሺ የነብዩን እጮኛ ማክበራቸውና መኽሩንም በራሳቸው መክፈላቸው እንዲሁም የነጃሺ ባለቤቶች ዑሙ ሀቢባ የተባለችው የነብዩ መሐመድ እጮኛን በተለያዩ ስጦታዎች ማንበሽበሻቸው ከሌሎች ሀገሮች በተለየ የሐበሻ ታላቅነትና ክብር የሚገለጽባቸው ነጥቦች ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ የዓለም ሕዝብ ወደ ስምንት ቢሊዮን እንደሚጠጋ የሚገመት ሲሆን፤ የሙስሊሙ ሕዝብ ቁጥር ሁለት ቢሊየን ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። ያለምንም ማጋነን የፖለቲካ ጉዳይ ችግር ካልሆነበት በስተቀር አብዛኛው የዓለማችን ሙስሊም ሕዝብ የአላህ ቃል በሆነው በቅዱስ ቁርዓን እና በነብዩ መሐመድ ንግግሮች ስለፍትሐዊነቷ የተመሰከረላት ሐበሻን (ኢትዮጵያን) መጎብኘት ይፈልጋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች በመላው ዓለም የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች እንዲያውቋቸውና ለኢትዮጵያ ተገቢውን ክብር እንዲሰጡ ማድረግ ይጠበቅብናል። ከቱሪዝም እድገት በተጨማሪ ለዲፕሎማሲያችን መሻሻልም ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

ኢትዮጵያ ለእስልምና ሃይማኖት ያበረከተችውን አስተዋጽዖ ያልዘነጉና ለዚህም ክብር የሚሰጡ የዓረብ ዓለም አገራት እንዳሉ ሁሉ፤ ጥቂት የማይባሉ አገራት ደግሞ ከኢትዮጵያ ጎን መሰለፍ ሲገባቸው ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ ባለችበት ወቅት ሲርቋት ታይተዋል። ከመራቅም አልፈው ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በመሆን በተለያዩ መንገዶች ኢትዮጵያ ላይ ያልተገባ ጫና እንዲደረግ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እነዚህ አገራት የኢትዮጵያን ውለታ ዘንግተውት አይደለም ከኢትዮጵያ በተቃራኒ የቆሙት። ግብጽ እኛ ኢትዮጵያውያን ተፈጥሮ የለገሰችን የአባይ ወንዛችንን ገድበን እንዳንጠቀም ለማድረግ ስትንቀሳቀስ የኢትዮጵያን ውለታ ወይም “ሐበሾች ሳይነኳችሁ አትንኳቸው!” የሚለው የነብዩ መሐመድን ንግግር ረስታ አይደለም። ሳዑዲ አረቢያ ዜጎቻችን ስታሰቃይና ከአገሯ ስታስወጣ የኢትዮጵያን ውለታ ወይም የነብዩ መሐመድን ንግግር ጠፍቷት አይደለም። ሱዳን እንኳን በአቅሟ ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ የገባችበትን ወቅት ጠብቃ የኢትዮጵያን ድንበር ጥሳ በመግባት መሬታችንን ስትወር ነብዩ መሐመድ ስለሐበሻ የተናገሩትን አጥታው አይደለም። ከላይ የተጠቀሱን የሦስቱ አገራት ድርጊት የአላህ ቃል የሆነውን ቁርዓንና የነብዩ መሐመድን ንግግር (ሐዲስ) የጣሰ እንዲሁም ኢትዮጵያ ለእስልምና የዋለችውን ውለታ ያላገናዘበ ነው።

ከላይ የተጠቀሱ አገራት ችግር እውነታውን አለማወቃቸው ሳይሆን “አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም” እንደሚባለው የግል ፍላጎታቸው ጆሯቸውን ስለደፈነው ከእውነትና ከታሪክ ጋር እንዲጣሉ አድርጓቸዋል። ሆኖም ግን ያለመሰልቸት እውነታውን ከማሳወቅ አንጻር ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራበት ይገባል።

እንደ አጠቃላይ ከላይ ከተጠቃቀሱ ነገሮች ጋር ተደምሮ የነብዩ መሐመድ ቤተሰቦችና ታላላቅ ባልደረቦች ለበርካታ ዓመታት በአገራችን መኖራቸው ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት የተለየች ያደርጋታል። በመሆኑም በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ ሙስሊሞች ለኢድ ሰላት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ “ከኢድ እስከ ኢድ” (ከኢድ አል-ፊጥር እስከ ኢድ አል-አድሃ) በሚል መሪ ቃል በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የቀረበው ጥሪ ኢትዮጵያ ለእስልምና ኃይማኖት ያበረከተችውን አስተዋጽዖ ለመላው ዓለም ከማሳወቅ አንጻር ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# የሕዝብ አገልግሎት መስጫ መተግበሪያዎች የሳይበር ጥቃት

**ዳግም ከበደ**

የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓታቸውን በዲጂታል አማራጭ ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ ጥረቶች እያደረገ መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገልፃል። ለፈጣን፣ ወጪ ቆጣቢና ቀልጣፋ አገልግሎት በዓለም ላይ ቀዳሚውን ስፍራ እየያዘ የሚገኘውን ይህን ሥርዓት መከተል ጊዜውን የሚዋጅ እንደሆነም የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ይሁን እንጂ የዲጂታል ሥርዓት ከሚሰጣቸው አያሌ ጥቅሞች ባሻገር በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር የማይቻል ከሆነ መዘዙ የዚያኑ ያህል እንደሆነ ነው የሚገለፀው። ለመሆኑ ይህን የአራተኛው ትውልድ የበይነ መረብና ቴክኖሎጂ ሥርዓት በምን መልኩ ማስተዳደር ይኖርብን ይሆን? ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገርስ ምን አይነት አሉታዊ ጎኖች አሉት? ይህን ጥያቄ እንደሚከተለው ለመመለስ እንሞክር።

ከሰሞኑ ዓለም አቀፍ የጥናት ተቋማት ይፋ እንዳደረጉት 82 ከመቶ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚጠቀሙባቸው ዲጂታል መተግበሪያዎች የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት አለባቸው። ይህ ማለት ከአምስት የሕዝብ አገልግሎት ሰጪዎች ከሚጠቀሙባቸው መተግበሪያዎች መካከል ከአራት በላይ የሚሆኑት የሳይበር ጥቃት ተጋላጭ እንደሆኑ ነው መገንዘብ የሚቻለው። ይህን ጥናት ይፋ ያደረገው ቬራኮድ የተሰኘ በዘርፉ ላይ በርካታ ምርምርና ጥናቶችን የሚያደርግ ካምፓኒ ነው።

ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ሲነጻጸር ለመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች ጥቅም ላይ የዋሉ መተግበሪያዎች ላይ የተገኙ ክፍተቶችን ለመጠገን በእጥፍ የመጠገኛ ጊዜ እንደሚጠይቅ ነው ተመራማሪዎቹ የሚናገሩት።

ከዚህ ባሻገር 60 በመቶ የሚሆኑት የሕዝብ ቤት መጽሐፍት ላይ የሚገኙ ክፍተቶች ሳይጠገኑ እስከ ሁለት ዓመት እንደሚቆዩም ይፋ ሲሆን ይህ ጊዜም ከሌሎች ሴክተሮች አንጻር ሲታይ እጥፍ ጊዜያት እንደሚቆይ እና ከአጠቃላይ ሲታይ ደግሞ እስከ 15 ወራት የተራዘመ ጊዜ የሚጠይቅ ነው። ጥናቱ በዋናነት በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ፣ በማኑፋክቸሪንግ ፣በፋይናንስ አገልግሎቶች ፣በተለያዩ ምርቶች ችርቻሮ ላይ ባሉ ዘርፎች ፣ በሆቴል ፣ በጤና አጠባበቅ እና በቴክኖሎጂ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ተግባራዊ ከሆኑ ግማሽ ሚሊዮን መተግበሪያዎችን ከ20 ሚሊዮን በላይ መረጃዎች ላይ ያተኮረ ነው።

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የሳይበር ጥቃት በመንግሥትም ሆነ በግል ተቋማት ላይ በእያንዳንዷ ደቂቃ ይሞከራል። ይህን ተከትሎ የሚወሰደው የሕግ ማስከበር እርምጃ ግን እጅግ አዳጋች እንደሆኑ ነው ጥናቶች የሚያሳዩት። ለዚህ እንደ ምክንያት ከሚቀርቡት ምክንያቶች አንዱ ጥቃት አድራሾቹ (ሃከሮች) ድርጊቱን በርቀትና እጅግ በረቀቀ ቴክኖሎጂ ስለሚፈፅሙት ነው። ይሁን እንጂ አሁንም ድረስ በዓለም አቀፍ ጥምረት አማካኝነት ወንጀለኞቹን በቁጥጥር ስር ለማዋል ይሞከራል። ይህንን በምሳሌ ለማየት እንዲያመቸን በቅርቡ የሳይበር ወንጀለኞች ላይ የተወሰደውን እርምጃ በጥቂቱ ለማየት እንሞክራለን።

ከሰሞኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከፈተ የሳይበር ወንጀለኞች የማደን ዘመቻ 65 በቢዝነስ ኢ-ሜይል ጥቃት ወንጀል ተሳትፈዋል የተባሉ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን ዓለም አቀፉ የሕግ አስከባሪ ጥምረት ይፋ አድርጎ ነበር። የቢዝነስ ኢሜይል ጥቃት አድራሾችን ለማደን ኦፕሬሽኑ በመስከረም ወር 2021 የተጀመረ ነበር። ኦፕሬሽን ኤግል ስዊፕ በሚል በተካሄደው ወንጀለኞችን የማደን ዘመቻ በሶስት ወራት ውስጥ 65 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን ተጠርጣሪዎቹ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተቋማት ላይ የኢሜይል ጥቃት አድርሰዋል። ከተጠርጣሪዎች መካከል ከናይጄሪያ 12፣ ከደቡብ አፍሪካ ስምንት ፣ ከካናዳ ሁለቱ እና አንድ ደግሞ ከካምቦዲያ ናቸው። ከዚህ ሪፖርት መረዳት የምንችለው ጥቃት አድራሾቹ ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸውና ርቀት የማይገድባቸው መሆኑን ነው።

ሌላው የአሜሪካው የወንጀል ምርመራ ቢሮ (FBI) ሪፖርት እንደሚያሳየው ባለፈው በፈረንጆቹ 2021 ዓመት በቢዝነስ ኢ-ሜይል አማካኝነት በተሰነዘረ የሳይበር ጥቃት 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ተቋማትን ያስወጣ ሲሆን ይህ መጠን ከ2020 ዓመት ከደረሰው ኪሳራ ጋር ሲነጻጸር በግማሽ ቢሊዮን ዶላር ያደገ መሆኑን ሪፖርቱ ያመላክታል። በተለይ ከሳይበር የሳይበር ወንጀል ኪሳራ ውስጥ በቢዝነስ ኢ-ሜይል የሚደርስ ጥቃት አንድ ሶስተኛውን ይሸፍናል።

ይህንን ሪፖርት አስመልክቶ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ባወጣው የማስጠንቀቂያ መልዕክት ከዚህ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሯል፤ የቢዝነስ ኢ-ሜይል ጥቃት የፋይናንስ ዘርፍን በከፍተኛ ደረጃ ለጉዳት ከሚዳርጉ የሳይበር ጥቃቶች መካከል አንዱ ነው። የመረጃ መንታፊዎች አብዛኛዎቻችን ኢ- ሜይልን ለተለያዩ ግላዊም ሆነ ተቋማዊ አገልግሎቶች መጠቀማችንን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ በኢ-ሜይል መልዕክቶች አማካኝነት የተለያዩ የሳይበር ጥቃቶችን እያደረሱ ይገኛሉ። በመሆኑም ማንኛውም የኢ-ሜይል ተጠቃሚ አጥፊ ተልዕኮ ባላቸዉ የኢ-ሜይል መልዕክቶች አማካኝነት ሊፈጸሙበት የሚችሉትን የሳይበር ጥቃቶች ለመከላከል ወደኛ አካውንት የሚላኩ ኢ-ሜይሎችን ትክክለኛነት ሳናረጋግጥ ከመክፈትም ሆነ ምላሽ ከመስጠት መቆጠብ ይገባል።

## በኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንና ስጋቶቹ

በመግቢያችን ላይ ለማንሳት እንደሞከርነው የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን በዲጂታል ሥርዓት ለመቀየር መንግሥት ሰፊ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። ከዚህ በተጓዳኝም ቴክኖሎጂውን ተከትሎ ሊከሰት የሚችል ስጋቶች እንደሚኖሩና እነርሱን ለመከላከል መከናወን ስላለባቸው ተግባራትም ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የዲጂታል ሽግግር ሂደቱ ምን መልክ እንዳለው በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክርና የጥንቃቄ እርምጃዎችን በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን እናነሳለን ።

በአገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ እድገት ላይ ሰፊ ድርሻ መውሰድ እንዳለባቸው ይታመናል። በተለይ ብቁ የሰው ኃይል ከማፍራት ባሻገር ትላልቅ ምርምሮችና የፈጠራ ግኝቶች መፈጠሪያም ናቸው። ለመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ መንግሥት በዲጂታል ሽግግር ዙሪያ የሚያደርገውን ጥረት ከመደገፍ አንፃር ምን ሚና እየወሰዱ ይሆን? ይህን ለመመለስ እንዲያስችለን የጎንደር ዩኒቨርስቲን በምሳሌነት እንጥቀስ።

ከቀናት በፊት "የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለሁሉ አቀፍ እና አካታች ልማት" በሚል ርዕስ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ አንድ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ውይይት ላይ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ "ጊዜው በዲጂታል ምሕዳሩ ላይ በጋራ ልንሠራበት የሚገባ ነው" በማለት አስተዳደሩ በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ከሚሠሩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ መንግሥታዊ እና የግል ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት እንደሚፈልግ አሳውቀው ነበር። ይህን ተከትሎ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አስራት አጸደወይን የዲጂታል ምህዳሩ በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያየ መልኩ የማይተካ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ገልፀዋል።

የዲጂታል ምሕዳሩን በመጠቀም በአገራችን ላይ የተሰነዘረውን የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ለመከላከል የዲጂታል አማራጭ የሆኑትን የማኅበራዊ ትስስር ገጾችን በመጠቀም ከሕግ ማስከበር እና የህልውና ዘመቻውን ለመመከት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት መቻሉንም ያስረዳሉ። በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዘርፉም ሆነ እንደ አጠቃላይ በሳይበር ደህንነት ዙሪያ በልዩ ሁኔታ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር ሥራዎችን በትብብር እየሠሩ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

ከሁለቱ ኃላፊዎች መረዳት እንደምንችለው መንግሥት የዲጂታል ሽግግር ለማድረግ ከሚሠራው ሥራ በተጓዳኝ ብቁ የሰው ሃብት ልማት ላይ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር እንደሚተባበር ነው። ይሁን እንጂ ዓለማችን እጅግ በረቀቀ የሳይበር ጥቃት ላይ ታላላቅ መንግሥታትን የሚያስጨንቁ የቴክኖሎጂ ቀበኛ ወንጀለኞች በበዙበት በዚህ ዘመን ዲጂታል ሽግግሩንና ደህንነቱ ላይ ጥብቅ ትስስርና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በመንግሥትም ሆነ በግል የሚመሩ ተቋማት የሚሰጧቸው የሕዝብ አገልግሎቶችና አገልግሎቱ ለማሳለጥ የሚረዱ ዲጂታል መተግበሪያዎች ለመንታፊዎችና ወንጀለኞች መጋለጥና ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ የሚከተሉት የጥንቃቄ ተግባራት ሊወሰዱ ይገባል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በበይነ መረብ የአጠቃቀም ክፍተቶችን እና የግንዛቤ እጥረት ሳቢያ ማኅበራዊ እና ስነልቦናዊ ቀውሶች እየጨመሩ መጥተዋል። ከዚህ ባለፈ ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ታላላቅ አገራትን ጨምሮ ዓለማችን በሳይበር ጥቃት አድራሾች ከፍተኛ ኪሳራ እያስተናገደች ትገኛለች። ይህ እንቅልፍ የሚነሳ ወንጀል የአንድን አገር ዋና ዋና ዘርፎች ከጥቅም ውጪ አድርጎ ለጥፋት እስከመዳረግ የደረሰ አቅም ያለው ነው። ለዚህ ነው አገራት የዲጂታል ሽግግር ሲያደርጉ ጎን ለጎን የቁጥጥር ሥርዓታቸው ጥብቅና የማይበገር መሆን እንዳለበት የሚታመነው።

## ለመሆኑ ጥቃት አድራሾች ዓላማቸውን ለማስፈፀም ምን አይነት አማራጮች ይወስዳሉ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሶሎሞን ከአጠቃቀም ክፍተት ጋር በተያያዘ ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር ትንኮሳዎችን መለየት እና መከላከል ያስፈልጋል ይላሉ። ተቋማቸው ግንዛቤ ለመፍጠር በተለያዩ አማራጮች ለጥንቃቄ ሊወሰዱ ስለሚገቡ መፍትሔዎች እንደሚጠቁም ገልፀው በአገር ላይ የሚደርስ ጥቃትን ለማስቆምም እንደሚሠራ ይናገራሉ። ሆኖም በኦንላይን የሚሰነዘሩ ጥቃቶች እና ትንኮሳዎችን መከላከል ለአንድ ተቋም ብቻ የሚተው እንዳልሆነ ነው የሚያስረዱት። "ሁሉን አቀፍ እና አካታች የዲጂታል ሽግግር" ለማድረግም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ነው የሚገልፁት።

## የዲጂታል ሽግግር ላይ የዜጎች ድርሻ

የበይነ መረብና አያሌ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሰው ልጅን እርቀት እንዳይገድበው ከማድረግ ባሻገር ሊታሰብ በማይችል የስልጣኔ መራቀቅ ውስጥ እንዲራመድ አስችለውታል። ይሁንና በተደጋጋሚ በርዕስ ጉዳያችን ላይ በወፍራሙ ለማስመር እንደሞከርነው ይህ ሥርዓት መልካም ነገሮችን ብቻ ይዞ የመጣ አይደለም። በተለይ ከግላዊነትና የመረጃ ደህንነት ጋር ተያይዞ ስጋትን ደቅኖ ይገኛል። በዚህም የመንግሥትና የግል ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ዜጎች ተጋላጭ ናቸው። በተለይ የግል የፋይናንስ መረጃዎችን ጨምሮ በርካታ ሰነዶች በመዝባሪዎች አማካኝነት ከዜጎች እጅ ሊመነተፉ ይችላሉ። ይህም መንግሥት የዜጎችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያደርገው ጥረት ላይ እንቅፋት መፍጠሩ የማይቀር ነው። የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት ሲመዘበሩም በዚያ ውስጥ ዜጎች ተጎጂ አይሆኑም ማለት አይቻልም። ከዚህ የተነሳም የሚከተሉትን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ባለሙያዎች ይመክራሉ። እኛም እነዚህን ጥቂት ነጥቦች አንስተን ሃሳባችንን እንቋጫለን።

በሶፍትዌሮች ውስጥ ያሉ ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ ክፍተቶችን "ባክዶር" እንደሚባሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለመሆኑ ይህን ክፍተት እንዴት መለየትና መከላከል እንችላለን? በምንጠቀምባቸው የሶፍትዌር ውስጥ ስውር እና ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ ክፍተቶችን ምልክቶች ሳያሳዩ ወይም ለኮምፒውተር ደህንነት ሥርዓት የማይታዩ በድብቅ የተለያዩ ተግባራት ማከናወን የሚችሉ በመሆናቸውና እንደ ማንኛውም ፕሮግራም ምንም አይነት መሠረት የሌላቸው መሆናቸው "ባክዶሮችን" መለየትን ውስብስብና ከባድ ቢያደርጋቸውም የሚከተሉትን ምልክቶች በማስተዋል የባክዶሮች ጥቃቶችን መለየት እንደሚቻል የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር መረጃ ይጠቁማል፡፡

የመጀመሪያው "ታስክ ማናጀርን" በመክፈት የኮምፒውተርዎን "CPU" እና "Memory" ከበስተጀርባ የሚጠቀሙ አጠራጣሪ አፕሊኬሽኖች ካገኙ ባክዶሮች ሊሆኑ እንደሚችሉም ይህ መረጃ ያረጋግጣል።

ለዚህ እንደ መፍትሔ ከተጠቆሙት መካከልም የዘመነ ትክክለኛ የፀረ-ቫይረስ መጠቀም፣ በየጊዜው ኮምፒውተርዎን መቃኘት፤ ከታመኑ ምንጮች ብቻ ማስፈንጠሪያዎችን መክፈት፤ አውታረ መረብ ላይ ክትትል ማድረግ ይገኙበታል።

**በአገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ እድገት ላይ ሰፊ ድርሻ መውሰድ እንዳለባቸው ይታመናል። በተለይ ብቁ የሰው ኃይል ከማፍራት ባሻገር ትላልቅ ምርምሮችና የፈጠራ ግኝቶች መፈጠሪያም ናቸው።**

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነቱን እንዴት እንከላከል?

**ታምራት ተስፋዬ**

ኢትዮጵያ ውስጥ ከዕለት ወደ ዕለት ኑሮ እየተወደደ፤ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የተለያዩ ሸቀጦች ዋጋ በእጅጉ እየጨመረ መጥቷል። ትናንት የተገዛ ዛሬ፣ጧት የገዛነው ከሰዓት ዋጋው መጨመሩም በርካቶች የሚያስጨንቅ ጉዳይ ከሆነም ዋል አደር ብሏል።

ቸርቻሪው ስለ ዋጋው መጨመር ሲጠየቅ ‹‹የለም ከማለት እንጂ እኔም በውድ ገዝቼ ነው››ያመጣሁት ሲል ይደመጣል።አከፋፋዩ ሲጠየቅ ‹‹አምራቹ ነው የጨመረው››ይላል። አምራቹ ደግሞ ‹‹ጥሬ ዕቃ የለም፣ጥሬ ዕቃው የሚገባው ከውጭ ነው፣ መንግሥት ደግሞ ዶላር ሊሰጠን አልቻለም››ሲል ይደመጣል።

አንዳንድ የምጣኔ ሐብት ባለሙያዎችም በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ የሚስተዋለው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ምክንያቶች በርካታ መሆናቸውን ያስረዳሉ።የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም፣ከመሠረታዊ ፍጆታዎች ፍላጎት ማደግ ጋር የሚመጣጠን ምርትና ምርታማነት አለማደግ፣በአምራቾችና በሸማቾች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለመኖር፣ የውጪ ምንዛሪ እጥረትና የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም በዋነኛ ምክንያትነት ያነሳሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሸቀጦች ዋጋ መናር፣የሰላም መታጣት፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ መሠረታዊ የሆኑ የምጣኔ ኃብት መዋቅሮች አለመስተካከል፣በአገር አቀፍ ደረጃ ለታየው የኑሮ ውድነት ተጨማሪ ምክንያቶች ተብለው ይዘረዘራሉ።

የምጣኔ ሃብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ፣ በዓለም ላይ የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝና የራሲያ-ዩክሬን ጦርነት፣አሸባሪው ሕወሓት በከፈተው ጦርነት ምክንያትም በተለይ በአማራና በአፋር ክልሎች በቂ ምርት አለመመረቱና መንግሥትም ለኢኮኖሚ ወይም ለሌሎች መሠረተ ልማቶች ድጎማ የሚውል ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉ ለዋጋ ንረቱ መባባስ ሁነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

በአገሪቱ በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል የተፈጠረው አለመጣጣም ለዋጋ ንረቱ መሠረታዊ ችግር መሆኑን ጠቅሰው፤በግጭቶችና በድርቅ ምክንያት የተረጂ ቁጥር ማሻቀቡን ተደምሮ የኑሮ ወድነቱን ይበልጥ እንዳባባሰውም ያነሳሉ።

የዋጋ ንረት በበርካታ የአገሪቱ ዜጎች ኑሮ ላይ ትልቅ ተጽእኖ ቢኖረውም በተለይም ገቢያቸው ውስን የሆኑ ሠራተኞች፣ጡረተኞችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሠራተኞች ላይ የከፋ ጫና አሳድሯል። የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ፤‹‹አሁን ላይ በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የኑሮ ውድነት ሠራተኛው ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል።በተለይም ዝቅተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ላይ የኑሮ ጫናው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ››ይላሉ።

ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ በርካታ ድርጅቶች ለሠራተኞች የሚከፍሉት ደመወዝ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን የሚጠቁሙት አቶ ካሣሁን፤እነዚህ ሠራተኞች በሚከፈላቸው ደመወዝ ሕይወታቸውን መምራት አዳጋች እንደሆነባቸውም ይገልጻሉ።

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ዝቅተኛውን የደመወዝ ወለል የሚወስን ደንብና የደመወዝ ቦርድ ተቋቁሞ እንደ አገር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል መቀመጥ እንዳለበት የሚጠቁሙት ፕሬዚዳንቱ፤ አዋጁ የወጣው ከሁለት ዓመት በፊት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ደንቡ ወጥቶ ወደ ሥራ አለመግባቱም ይገልፃሉ። ይህም ችግሩ መፍትሄ እንዲርቀው ማድረጉን ያሰምሩበታል።

ምሑራንም ምክንያቶቹን ከመዘርዘር ባሻገርም ችግሩ የሚገባውን ትኩረትና ፍቱን መፍትሔ ማግኘት እንዳልቻለ በመግለፅ መንግሥትም ወጥ የሆነ ቁርጠኝነት አይስተዋልበትም ሲሉም ይተቻሉ። በዚህ ወቅት ያለው ትልቁ ችግር የአቅርቦት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በገበያው ውስጥ የሰፈነው ሥርዓት አልበኝነት እንደሆነ አጽእኖት ይሠጣሉ።

መንግሥት በድጎማ የሚያመጣቸውን መሠረታዊ ሸቀጦች ሳይቀር በአግባቡ ለሸማቹ እየደረሱ ስለመሆናቸው ከላይ እስከ ታች መከታተልና መቆጣጠር እንዳልቻለ የሚጠቁሙት ምሑራኑ፣ምርቱን ማስገባት ብቻ መፍትሔ አለመሆኑን ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የታየ ችግር እንደሆነ ያነሳሉ።

በየቀኑ የሸቀጥ ዋጋ እየጨመረ በነፃ ገበያ ስም

> **በሕገ ወጥ መልኩ የተደበቀ የምግብ ዘይት በቁጥጥር ስር ዋለ ሲባል በዜና እንሰማለን፣ እናያለን፣ ይሑንና የደበቀው ማነው፣ፍርድ ቤት መቼ ቀረበ፣ ክስ ተመስርቶበትስ ምን ውሳኔ ተሳለፈበት‹‹ የሚል ዜና አንሰማም፣ አናይም፣ ባለፉት ዓመታት አንድም ለፍርድ የቀረበና የተፈረደበት ሕገ ወጥና ስግብግብ ነጋዴ አላየንም‹‹**

ሕዝቡ እየተበዘበዘ፣ ጥቂቶች እየበለፀጉ መሆኑን የሚገለጹት ምሑራኑ፣ነጋዴው በነፃ ገበያ ስም ሕዝቡ ላይ እንዳገኘ ዋጋ እየጨመረ የሚሄድበት አሠራር ከልካይ እንደሚያስልገውም ያስገነዝባሉ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማክሰኞ መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርን የስምንት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል። በእለቱ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረ መስቀል ጫላ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የዋጋ ንረትንና የኑሮ ውድነቱን ያባብሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ 104 ሺሕ የሚጠጉ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ በየደረጃው በተዋቀረ የዋጋ ማረጋጋት፣ ሕገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር ግብረ ኃይል በተደረገ ክትትል ሕጋዊና አስተዳደራዊ ዕርምጃ መወሰዱን ለፓርላማው ገልጸዋል።

አቶ ገብረ መስቀል የኑሮ ውድነቱን ለማባባስ በሕገወጦች ላይ በተደረገው ክትትል ሕጋዊና አስተዳደራዊ ዕርምጃ በመውሰድ ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት መደረጉን ቢገልጹም፣የፓርላማ አባላቱ በአንጻሩ፣‹‹የኑሮ ውድነቱን የሚያባብሱ ሕገወጦች ላይ ተገቢው እርምጃ አልተወሰደም፤ በዚህም የተነሳ የሸቀጦች ዋጋ መቆጣጠር አልተቻለም›› በሚል በሚኒስቴሩ ላይ የሰላ ትችት ሰንዝረዋል።

ሥልጣኑ በእጃችሁ እስካለ ድረስ ሕገወጦች ላይ አስተማሪ እርምጃ ለምን መውሰድ ተሳናችሁ? ሲሉ የጠየቁት የምክር ቤት አባላቱ፤ ሕገ ወጦቹ ተለይተውም አስተማሪ እርምጃ ሲወሰድባቸው የማናያቸው ለምንድ ነው ሲሉም ጠይቀዋል።

ሌላው ቀርቶ በድጎማ የሚገቡ ምርቶች ሳይቀር በአግባቡ ለኅብረተሰቡ እየተዳረሱ እንዳልሆነ በመግለፅ፣ ይህም የሆነው ተጠያቂነት ስለሌለና የግብይት ሥርዓቱን የሚመራ አሠራርና አደረጃጀት ባለመኖሩ እንደሆነ አንስተዋል።

የዋጋ ንረቱን ያባባሰው የመንግሥት የላላ ቁጥጥር እንደሆነም በርካቶች ይስማሙበታል።ምርት ደብቆ ወይም ከገበያ ዋጋ በላይ ሲሸጥ የተገኘ ነጋዴ የሚወሰድበት እርምጃ ምናልባት እስካሁን የምንሰማው ተወረሰ የሚል ዜና ነው።ማንም ነጋዴ እንዲህ በማድረጉ በፍትሕ ተጠይቆ ሲቀርብ ወይም ሲፈረድበት አይሰማም።ይኼ ደግሞ ሕገወጥነት እንዲስፋፋና እንዲበራከት አጋጣሚ ፈጥራል።

ይሕን እሳቤ የሕግ ባለሙያዎችም የሚጋሩት ነው።አቶ ኪያ ፀጋዬም እሳቤውን አጥብቀው ከሚጋሩ መካከል አንዱ ናቸው።‹‹ሌላው ቀርቶ በሕገ ወጥ መልኩ የተደበቀ የምግብ ዘይት በቁጥጥር ስር ዋለ ሲባል በዜና እንሰማለን፣ እናያለን፣ ይሑንና የደበቀው ማነው፣ፍርድ ቤት መቼ ቀረበ፣ ክስ ተመስርቶበትስ ምን ውሳኔ ተላለፈበት›› የሚል ዜና አንሰማም፣ አናይም፣ ባለፉት ዓመታት አንድም ለፍርድ የቀረበና የተፈረደበት ሕገ ወጥና ስግብግብ ነጋዴ አላየንም›› ይላሉ።

የሕግ ባለሙያው መንግሥት የኑሮ ውድነትን እና የጋራ ንረትን ፈር በማስያዝ ረገድ ሕግን በአግባቡ ለመተግበርና ለማስፈፀም ቁርጠኛ ከሆነ መሰል አስተማሪ የሕግ ውሳኔዎችንም በአደባባይ ሊያሳውቅ እንደሚገባም ያሰምሩበታል።

መጋቢት 29 ቀን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት በተዘጋጀው አዲስ ወግ መድረክም የኑሮ ውድነትን አብይ ጉዳይ ሆኖ ውይይት ተደርጎበታል። ‹‹የኑሮ ውድነት መንስኤዎቹ እና የመፍትሔ እርምጃዎች›› በሚል ርዕስ በተካሄደው በዚሁ ውይይትም ምሑራን ለችግሩ መንስኤ እና መፍትሔ የሚሉትን አቅርበዋል።

በዚሁ መድረክ ላይም በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የኅብረት ስራ ግብይት ዳይሬክተር ይርጋለም እንየው፣የኢትዮጵያ የግብይት ሰንሰለት የሚስተዋለው ርዝማኔ መሻሻል እንደሚያስፈልገው ነው ያስገነዘቡት። ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራዎች እየተከወኑና የኅብረት ሥራ ማኅበራትና በርካታ የሸማቾች ማኅበራት ቢኖሩም እሴት የማይጨምሩ ሕገወጥ የግብይት ተዋናዮች መኖራቸው ተገቢው የዋጋ ተመን እንዳይኖር አድርጓል ነው››ያሉት።

ችግሩን ለመሻገር ምርታማነትን ማሳደግ፣ የአቅርቦት ክፍተትን መሙላት፣ የአምራችና የኢንዱስትሪ ትስስርን ማጠናከር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አሠራር ማዘመን እና ሕገ ወጥ የግብይት ተዋናዮችን መቆጣጠር እንደሚያስፈልግም አጽእኖት ሰጥተውታል።

ምሑራንም፣በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የኑሮ ውድነት ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኝ ከቀጠለ አገሪቷን አስቸጋሪ የምጣኔ ኃብት ቅርቃር ውስጥ ሊያስገባት እንደሚችል ይስማሙበታል።ይህ እንዳይሆን ምን ይደረግ ለሚለውም መፍትሔ የሚሉት አላቸው።ከሁሉ በላይ መንግሥት የገበያ ሥርዓት ማስከበር፣ ሕገወጥ የገበያ ሰንሰለቱን መበጣጠስ እንዳለበት አጽእኖት ይሰጡታል።

የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት መንግሥት የአጭር የጊዜና የረዥም ጊዜ ተከታታይነት ያላቸውን ሥልቶች መቀየስ እንደሚጠበቅበት የሚያስገነዝቡት ምሑራኑ፣‹‹በአጭር ጊዜ መፍትሔዎች መንግሥት ጣልቃ በመግባት ምርቶቹን ከአምራቹ ወይም ከውጭ በማስመጣት ወደ ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲደርሱ ማድረግ ይኖርበታል››ይላሉ።

‹‹ዘይትና ስኳር በመሳሰሉ የማኅበረሰቡ አንገብጋቢ ጥያቄዎች የያዙና በምርት ሒደት ላይ ያሉ ድርጅቶችን፣ በሙሉ አቅም እንዲያመርቱ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ፤የዋጋ ንረት እየፈጠሩ ያሉ ነጋዴዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግና ሱቆችን ከማሸግ ጀምሮ፣የንግድ ፈቃድ እስከ መቀማት አስፈላጊን የሕግ እርምጃ መወሰዱንም በግልጽ ማመልከት፣በአንዳንድ ምርቶች ላይ የተተገበረው የቀረጥ ቅነሳ በሌሎችም ላይ ማድረግ የግድ ነውም›› ይላሉ።

የገንዘብ ሚኒስቴርም መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የሕጻናት ወተትና ሩዝ ያለምንም የውጭ ምንዛሪ ፍቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እንዲገቡ ሚያዚያ 1 ቀን 2014 ዓ.ም መወሰኑን አሳውቋል።መንግስት የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እንዲቻልና በርካታ የውጭ አገር የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሚና መጫወት እንዲችሉ የፍራንኮ ቫሉታ ፈቃድ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ እያቀረቡ በመሆኑ መወሰኑን ሚኒስቴሩ ገልጿል።

ቀረጥና ታክስን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/3/2013 ዓ.ም በቁጥር ማአ.30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም፤አፈጻጸሙን በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት ወስኗል።

ይሑንና ምሑራኑ፣ከመሰል እርምጃዎች ባሻገር የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ ከሁሉ በላይ ማክሮ ኢኮኖሚውን (macro Economic policy) ውን መፈተሽ ያስፈልጋል››ይላሉ።ይሕን እሳቤ የምጣኔ ሃብት ምሑሩ ዘመዴነህ ንጋቱ ይጋሩታል።አቶ ዘመዴነህ እየጨመረ የመጣውን የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመግታትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ፈትሾ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ያሰምሩበታል።ይህን እሳቤ በመንግሥት በኩልም ታምኖበታል።

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የተዛባውን የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ለማስተካከል የሶስት ዓመት እቅድ መዘጋጀቱን አሳውቋል።ከዚህ ቀደም የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቱ ምንጭ አገሪቷ አይናን ጨፍና የተበደረቻቸው ውድ ብድሮች ውጤታማ መሆን ሳይችሉ ቀርተው አገሪቱን የከፋ ሁኔታ ውስጥ መክተቱ ያስታወሱት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ፣አሁን ደግሞ በጦርነቱ ምክንያት የገጠመው የበጀት እጥረት የማክሮ ኢኮኖሚው መዛባት ምንጭ ሆኗል ነው ››ያሉት።

ሚኒስትሯ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር በነበራቸው ቆይታ፣በበጀት በኩል የሚመጣ መዛባትን ለመከላከል ፕሮጀክትን በሚገባ ማስተዳደርና ወጪን መቆጠብ በቀጣይ ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች መሆናቸውን ነው ያመላከቱት።

ኢኮኖሚው መሻገር ያልቻላቸው በርካታ ችግሮች እንዳሉበት በማንሳት ይህን ለማስተካከል ደግሞ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባ ዝርዝር እቅድ በማስፈለጉ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ የተቀዳ እና አሁናዊነትን የተጎናጸፈ የሶስት ዓመት እቅድ ማዘጋጀቱን አስታውቀዋል።‹፣በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት መተግበር የሚጀምረው እቅዱ ጥራት ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማስመዝገብ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን ዋነኛ ምሰሶው ያደረገ ነው››ብለዋል።

ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ባሻገር ለዋጋ ግሽበቱና ለኑሮ ወድነቱ አንዱ መንስኤ የሆነው የውጭ ምንዛሪ እጥረት መሆኑን የሚገልጹት አቶ ዘመዴነህ፣ አላስፈላጊ ግዥዎችንና የውጭ ምንዛሪን የሚሻሙ ተግባራቶችን መግታት የግድ ስለመሆኑም አጽእኖት ሰጥተውታል።በተለይም‹‹ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ባለባት አገር 25 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ መኪናዎችንና ውድ ሸቀጦች ወደ አገር ቤት እንዲገቡ መፍቀድ ተገቢ አይደለም››ይላሉ።

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ በጥቁር ገበያ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ከማድረግ ጎን ለጎንም በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚኖሩ ዳያስፖራዎች በሕጋዊ መንገድ ገንዘባቸውን ሲልኩ የተሻለ ምንዛሪ የሚያገኙበትን የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ ጠቃሚ ስለመሆኑም ነው አፅእኖት የሠጡት።

የገበያ ሥርዓቱም ሥራ ላይ ያሉ አንዳንድ ድንጋጌዎች በአመዛኙ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የነበሩ በመሆናቸውን አስታውሰው፤በዚህ ምክንያትም አስመጪና ላኪዎች በተወሰኑ ሰዎች የተያዘ በመሆኑ እንደሌሎች አገራት የሸቀጦችን ዋጋ የሚወስኑ ሸማቾች ሳይሆን እነዚህ ግለሰቦች መሆናቸውንም ይጠቁማሉ።በተለይ ሰው ሠራሽ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ምን ያህል ሸቀጦች እንደሚያመጡና በስንት ዋጋ እንደሚሸጡ በቴክኖሎጂ የታገዘ የቁጥጥር ሥርዓት መፍጠር እንደሚገባም ነው ያመላከቱት።

በዓለም ላይ የሸቀጦች የዋጋ ንረት በቀጣዩ ወራቶች የመጨመር አዝማሚያ እንደሚኖረው ታሳቢ በማድረግ መንግሥት በተቻለው መጠን በመሠረታዊ የፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚያደርገውን ድጎማ ማጠናከር እንደሚኖርበትም ነው ያስገነዘቡት።

የዋጋ ንረትንና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የግብርና የኢንዱስትሪ ምርትና ምታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤በተለይ መንግሥት በበጋ ስንዴ የጀመረውን ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ በሌሎች ምርቶችም ማስፋት ለነገ የማይባል ጉዳይ እንዳልሆነም አስምረውበታል።

‹‹ኢትዮጵያ ያላትን የመሬት ሀብት በአግባቡ ማልማት ከቻለች ዘይት ጨምሮ ለሌሎች አገራት የመላክ አቅም እያላት ከውጭ ዘይትና ስንዴ ማስገባቷ የሚያስቆጭ ነው››የሚሉት አቶ ዘመዴነህ፣የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ ትላልቅ መካናይዝ እርሻዎችን ማስፋት የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ወሳኝ ስለመሆኑም ሳይጠቁሙም አላለፉም።፣

በሌሎች አገሮች ልምድ ኑሮ ውድነቱ ሲጨምር ዝቅተኛ ደመወዝ ወለል እንዲሻሻል እንደሚደረግ የሚጠቁሙት የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ፣ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ማድረግ ይቻል ዘንድ የዝቅተኛ ደመወዝ ወለል መወሰኛ ደንብ በአፋጣኝ ወጥቶ ዝቅተኛው የደመወዝ ወለል እንዲቀመጥ መደረግ እንዳለበት ሳያስገነዝቡ አላለፉም።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የአንጋፋዋ ‹‹የባከነው ጊዜ›› ደራሲ ተሞክሮ

**ሰላማዊት ውቤ**

እችላለሁ ብሎ ራስን እንደማሳመን ያሰቡት ግብ ላይ የሚያደርስና ለስኬት የሚያበቃ ምስጢር እንደሌለ ብዙዎች ከራሳቸው ተሞክሮ በመነሳት ሲናገሩ ይደመጣል። አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ እንደሚለው "እችላለሁ!" ብሎ የተነሳ ማንኛውም ሰው ከሰማይ በታች ያቀደውን ከማሳካት ወደ ኋላ ሲል አልታየም። በዕቅዱም ቢሆን አፍሮ አያውቅም። ይሁን እንጂ አንዳንድ፣ እንደውም ብዙ የሚሰኙ ሴቶች "እችላለሁ" የሚል ቁርጠኝነት የላቸውም። ቢኖራቸውም በራሳቸውም ሆነ በማኅበረሰቡ አማካኝነት የተፈጠረ ተፅዕኖ ወደ ውስጣቸው ዘልቆ በመግባቱ በራስ መተማመናቸውን ሸርሽሮ ለስኬት እንዳይበቁ ያደርጋቸዋል። ቢበቁም ስኬታቸው ያሰቡበት ድረስ አስጉዞ ለግብ ሲያበቃቸው አይታይም።


እናም ‹‹የት ይደርሳል የተባለን ዛፍ ቀበሌ ቆረጠው›› እንደሚሉት ዓይነት መንደርኛ አባባል በአገራችን በየሙያ መስኩ ወይም በየጥሪና ተሰጧቸው ብዙ "የት ይደርሳሉ" ተብለው ይጠበቁ የነበሩ ሴቶች በአጭሩ ሲቀጩና የት እንዳሉ ለማወቅ እንኳን በማያስችል መልኩ ደብዛቸው ሲጠፋ ይስተዋላል። የዛሬ የአምዱ እንግዳችንና ‹‹የባከነው ጊዜ›› ልብ ወለድ መጽሐፍ ደራሲዋ መጠነወርቅ ሳሙኤል ከእነዚህ ሴቶች መካከል አንዷ ላለመሆን የባከነ ጊዜያቸውን በማካካስ ሲጥሩ የነበሩ በመሆናቸው ተሞክሯቸው ለሌሎች ሴቶች ያስተምራል የሚል እምነት አለ። በተለይ ሴት ደራሲ ቀርቶ ብዙ ፊደል የቆጠሩ ሴቶች በአገራችን ባልነበሩበት በ1965 ዓ.ም ‹‹የባከነው ጊዜ›› የሚለውን የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን ለማሳተምና ለሌሎች ሴቶች አርአያ ለመሆን መብቃታቸው እጅጉን ይደነቃል።

(መጽሐፉ (ባጭሩ) በአንድ ጣራ ስር ተጋብተው ወልደው ከብደው ለመኖር ውጥን በነበራቸው ሁለት ፍቅረኛሞች ታሪክ ላይ ያጠነጥናል። በመጽሐፉ ታሪክ ወጣቶቹ ጥንዶች ይሄን ውጥናቸውን ከስኬት ለማድረስም ብዙ ጥረት ሲያደርጉ ይታያል። በዚህ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይባክናል። ይሄን ጊዜ ለማካካስ የራስ ጥረት ወሳኝ መሆኑን ያመላክታል። በአጠቃላይ መጽሐፉ ቸኩሎ ወደ ፍቅር ሕይወት መግባትም ሆነ፤ ለረጅም ጊዜ በፍቅር ጓደኝነት መቆየት የየራሱ ጥቅምና ጉዳት ያለው መሆኑን በሚገባ ያስገነዝባል። የባከነውን ጊዜ ማካካሱ ለጉዳቱ ዓይነተኛ መፍትሔ መሆኑንም ይጠቁማል።)

ደራሲ መጠነወርቅ ሳሙኤል ዛሬ በ71 ዓመት ዕድሜያቸው ላይ ሆነውም ያኔ ያልተቋጨውንና የሁለቱን ወጣቶች የፍቅር ታሪክ ያካተተ ሁለተኛ ክፍል መጽሐፍ ጽፈው ለማሳተም መንገድ ላይ መሆናቸው፣ የሌሎች ድጋፍን መሻቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ የሚበረታታና ሌሎች ሴቶችን የሚያነሳሳ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም ሥራዎቻቸውን፣ ልምድና ተሞክሯቸውን ለአንባቢያን እነሆ ማለትን ወ'ደናል።

ደራሲ መጠነወርቅ ሳሙኤል በ1943 ዓ.ም ዱከም ከተማ ነው የተወለዱት። የተወለዱበት አካባቢ ልዩ ስሙ ዝቋላ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ይሰኛል። አባታቸው የዚሁ የመድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን የቆሎ ተማሪ በመሆን ከድቁና እስከ ቅስና የዘለቀ የክህነት እውቀትና ሙያ የቀሰሙ ነበሩ። መነሻቸውን ወሎ አድርገው ከክፍለ አገር ክፍለ አገር እየተዘዋወሩ የቆሎ ትምህርት በሚቀስሙበት አጋጣሚ ከእናታቸው ጋር ትዳር መስርተው የወለዷቸው ወላጅ አባታቸው ለትምህርት ልዩ ፍቅር ነበራቸው። በተለይም ባህላዊ፤ ከባህላዊም የቄስ ትምህርት ለዘመናዊ ትምህርት ጥሩ መሠረት ጥሎ እንደሚያልፍ የሚያምኑ ነበሩ። በመሆኑም ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዛው የተወለዱበት ዱከም ከተማ ውስጥ ቄስ ትምህርት ቤት እንዳስገቧቸውና ፊደል እንዳስቆጠሯቸውም አጫውተውናል። ቶሎ ማንበብና መጻፍ ከማስቻል ጀምሮ ለዘመናዊ ትምህርት ጥሩ መደላድል በፈጠረላቸው የቄስ ትምህርት እስከ ዳዊት መድገም በመዝለቅ ዕውቀት ቀስመውበታል።

በወላጅ አባታቸው የሥራ ፀባይ ምክንያት ከናዝሬት ዱከም፤ ከዱከም አዲስ አበባ ከተማ መዘዋወርና ትምህርታቸውን መማር ግድ የሆነባቸው ደራሲ መጠነወርቅ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን


የባከነው ጊዜ

ከመጠነወርቅ ሣሙኤል

ልብ ወለድ

አዲስ አበባ.....፲፱፻፷፭ ዓ. ም.

አሀዱ ብለው የጀመሩት ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በዳግማዊ ምኒልክ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት እንደሆነም አጫውተውናል። በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በፅዳትነት ተቀጥረው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ወላጅ አባታቸው እሳቸውን ዳግማዊ ምኒልክ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዳስገቧቸውም ነግረውናል።

‹‹ይህ ትምህርት ቤት በቄስ ተማሪነቴ የቀሰምኩት ትምህርት ብቁ እንዳደረገኝና መሠረት እንደጣለልኝ ያየሁበት ነው›› የሚሉት ደራሲዋ፣ በተለይ አንደኛና ሁለተኛ ክፍል ሆነው በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን በፍጥነት ጽሑፍ የማጻፍና የማስነበብ ተግባር ማከናወናቸው አስደናቂ ከሂሎት አስጨብጧቸው የነበረ መሆኑንም ያስታውሳሉ። ‹‹ክፍል ውስጥ ሰርክ አርብ አርብ በነበረው የንባብ መርሐ ግብር ተማሪዎችን በማስነበብና በማጻፍ ወደር ያልተገኘልኝ ተማሪ እንድሆን ረድቶኛል›› ሲሉም ዕውቀት ያስጨበጣቸውን የቄስ ትምህርት ይመሰክሩለታል። በ1965 ዓ.ም ‹‹የባከነው ጊዜ››ን እንዲጽፉ መሠረት የጣለላቸው ይሄው የቄስ ትምህርት መሆኑንም በኩራት ይጠቅሳሉ።

‹‹ማትሪክ ብቻ ሳይሆን የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናም የሠራለትን አያውቅም›› የሚሉት ደራሲዋ በዘመናዊው ትምህርት እስከ ስምንተኛ ክፍል ዘልቀው የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ሳያልፉና ሁለተኛ ደረጃ የሚያስገባ ነጥብ ለማምጣት ሳይችሉ መቅረታቸውንም በቅሬታ ይገልፁታል። ራሳቸውን በትምህርት እያሻሻሉ መጥተው ከጽዳት እስከ ሂሳብ ሹምነት በመዝለቅ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በሂሳብ ሰራተኛነት የሚሰሩት የቆሎ ተማሪው አባታቸው ፈተናውን ደግመው በመውሰድ ያሰቡበት የሚደርሱበት ሰፊ ዕድል እንዳላቸው ደጋግመው ቢመክሯቸውም መጠነወርቅ በጄ አላሉም። ከጓደኞቻቸው መለየታቸው ስለቆጫቸው ፈተናውን ደግመው መውሰድ ጊዜያቸውን ማባከን ሁሉ አድርገውት ነበር። በመሆኑም በኋላ ላይ እጅግ የጓጉለትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል በመዝለቅ ለማጠናቀቅ ቢበቁም የባከነ ጊዜቸውን በአቋራጭ በመቅደም ከአሰቡት ለመድረስ ወደ ሙያው ትምህርት ማዘንበልን መረጡ።

መጠነወርቅ "ብርሃነ ኢትዮጵያ" የተሰኘ ትምህርት ቤት በመግባትም በፀሐፊነትና በአካውንቲንግ ሙያ በመሰልጠን ከ10ኛ ክፍል ተመረቁ። የቀድሞው ንግድ ሥራ ኮሌጅ በመቀጠርም በጽሕፈት ሙያ (ሴክሬተሪነት) የሥራ ላይ ስልጠና ወሰዱ። ከዚሁ ጋርም በሂሳብ ሥራ መሥራት የሚያስችላቸውን ዕውቀትም አካተው ቀሰሙና በ1961 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሥራ ዓለም ለመሰማራት በቁ። ወደ እዚህ ውሳኔ ለማምራታቸው ያኔ የነበሩበት የእሳቸውና


ደራሲ መጠነወርቅ ሳሙኤል
አሁን ላይ ከባለቤታቸው ጋር
የሚገኙበት ሁኔታ

የፍቅረኛቸው ሁኔታ አስተዋጽዖ ተፅዕኖም አርጎባቸው እንደነበረም አልሸሸጉንም ደራሲዋ። እንዳወጉን አንዳቸው ለአንዳቸው መስዋዕትነት እየከፈሉ ነው እዚህ የደረሱት። መስዋዕትነቱ ትምህርት አቋርጦ ወደ ሥራ ዓለም በመግባት በትዳር ተጣቃልሎ እስከ መኖር ታሳቢ ያደረገ እንደነበርም ነግረውናል። በተለይ ባለቤታቸው 12ኛ ክፍል ፈተና ወስደው ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባት ይልቅ በሥራ ተሰማርቶ ከእሳቸው ጋር ትዳር መስርቶ እስከ መኖር የዘለቀ መስዋዕትነት መክፈላቸውን ይናገራሉ። ከዚህም ጥቂቱን ለመጻፋቸው እንደማጣፈጫ መጠቀማቸውንም ገልጸውልናል።

አንጋፋ ደራሲዋ በዋነኝነት መጽሐፉን ለመጻፍ ያነሳሳቸው ፈጣንና ጥልቅ አንባቢ ለመሆን መሠረት የጣለላቸው በአባታቸው ምርጫ የቀሰሙት የቄስ ትምህርት እንደ ነበር ደጋግመው አጫውተውናል። በዚህ አነሳሽነት በተለይ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በጸሐፊነት ተቀጥረው በሚሠሩበት ወቅት ጥሩ መጽሐፍ አንባቢ ለመሆን መብቃታቸው እንደሆነም ሳይጠቅሱልን አላለፉም ደራሲዋ። ወደ ኋላ ታሪካቸው መለስ ብለው ስለ ድርሰት ፍቅር ተስጥኦዋቸው እንዳጫወቱን አብዛኛውን ደሞዛቸውን መጻሕፍት ለመግዛት ነበር የሚያውሉት። አዳዲስ መጽሐፍ በወጣ ቁጥር ቢሯቸው ድረስ ይዘውላቸው ከች የሚሉ ደንበኞችም ነበሯቸው።

ደራሲ መጠነወርቅ ‹‹የባከነው ጊዜ›› የሚል ርዕስ የሰጠሁትን ረጅም ልቦለድ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ይሄ ሁሉ ተደማምሮ ነው›› ሲሉም ነው ያጫወቱን። በወቅቱም እጅግ ተወዳጅነትን አትርፎ እንደ ነበር፤ ገበያ ላይ ውሎም በገፍ ለመሸጥ መብቃቱን ገልፀውልናል።

ደራሲ መጠነወርቅ እንደሚሉት ከ‹‹የባከነው ጊዜ›› በኋላ ከድርሰት ዓለም ለረጅም ጊዜ ተለዩ። ይህም በአንባቢና አድናቂዎቻቸው ዘንድ መዘንጋትን አስከተለ። ይህንን ክፍተት በመጠቀምና እንደ እሳቸው መጽሐፍ ተወዳጅ ይሆንልኛል በማለት አንዲት ሴት ‹‹የባከነ ጊዜ›› የሚል የእሳቸውን ርዕስ በመስጠት መጻፍ በማውጣት አሳትማ እንደ ነበር በአግራሞት ይናገራሉ።

በወቅቱ በጥንዶች ፍቅር፣ ታሪክና ሕይወት ላይ የሚያተኩረው የረጅም ልቦለድ መጽሐፋቸው ለእሳቸውም ትልቅ ከበሬታ፣ አድናቆትና ተወዳጅነትን


ደራሲዋ ወት/ መጠነወርቅ ሣሙኤል ።

ይህች መጽሐፍ ሰኔ ፪ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. የጋብቻቸውን አሥረኛ ዓመት ለሚያከብሩት በማንከባከብ አስተምረውና ከዚያም ፍላጐቴ ወደ ሥራ ባደላበት ጊዜ ሥራ ፈልገው በማስያዝ ፤ አሁንም ካንዱ ልጃቸው እኩል በማየት ሰብስበው ለያዙኝ ለአቶ ልዑል ሰገድ አስፋውና ለወይዘሮ ማራ ሣሙኤል ስጦታ የተዘጋጀች ነች ።

መ. ሣ.

— ፫ —

አስገኝቶላቸው አልፏል። በአንባቢያኑ ዘንድ "ሌሎች ረጃጅም የልቦለድ መጻሕፍቶችን ይዛ ትመጣለች" በሚል ተስፋ ሲያስጠብቃቸውም ቆይቷል። ደራሲና ገጣሚ የዝና ወርቁ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፏን በዚህ መጽሐፍ ላይ ነው የሠራችው። ሆኖም ብዙዎቻችን እንኳን ሌሎች የደራሲዋን የረጅም ልቦለድ መጻሕፍቶች ልናይና ልናነብ እንዲህ አይነት፣ ከጊዜው የቀደመች እንስት ስለመኖሯም ሳናውቅ ቆይተናል።

ደራሲ መጠነወርቅ ሳሙኤል እንደሚሉት ሌሎች መጻሕፍቶችን ለሕትመት ያለማብቃታቸውና ደብዛቸው የመጥፋቱ ምክንያት ፈርጀ ብዙ ቢሆንም፤ ‹‹የባከነው ጊዜ›› የተሰኘውንና ታሪኩ ያልተቋጨውን መጽሐፋቸውን ተከታይ ክፍልና ሌሎች ሥራዎቻቸውን ይዘው ብቅ የማለት ውጥን እንደነበራቸው ያወሳሉ። ነገር ግን የቢሮ ሥራ ጫና፣ ትዳር መያዝ፣ ልጆች መውለድና የቤተሰብ ኃላፊነቶችን መሸከም እንዲሁም በነዚህ መካከል የሚገጥሙ መሰናክሎች ምክንያት ውጥናቸው ከግብ ለመድረስ ሳይችል ቀርቶ መኖሩንም አብራርተውልናል። ለዚህ ውጥናቸው መሰናከል ዋንኛ ምክንያት ነው የሚሉት ይህንን ሁሉ ተቋቁመው በቁርጠኝነት አለመነሳታቸውን ሲሆን፤ ሌሎች ለእንደዚህ አይነቱ ችግር እጅ እንዳይሰጡም ይመክራሉ።

‹‹ምንም እንኳን እኔ የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና ወስጄ ውጤት ሳይመጣልኝ በመቅረቱ ወደ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ፊቴን በማዞር ለማካካስ ብሞክርም የመጀመሪያው ተከታይ የሆነውን መጽሐፌንም ሆነ ሌሎች ልጽፋቸው የሚገቡ መጻሕፍትን ሳልጽፍ መቅረቴ እችላለሁ ብዬ ያለመነሳቴ ድክመት ውጤት እንደሆነ አስባለሁ›› ብለውናል ደራሲዋ። ይሄ ዓይነቱ ድክመት በሌሎች የእሳቸው መሰል ተሰጥኦ ባላቸውም ሆነ በሌሎች ሴቶች መደገም እንደሌለበትም ደጋግመው ያስጠነቅቃሉ።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሴቶች ያሰቡትን ዳር ለማድረስና ለስኬት ለመብቃት ‹‹እችላለሁ›› የሚለውን መንፈስ በውስጣቸው ማዳበር እንደሚገባቸው በቴሌቪዥን መስኮት ደጋግመው ሲናገሩ መስማታቸውንና ይሄም የራሳቸውን ክፍተት እንዲያዩ እንዳደረጋቸው ደራሲ መጠነወርቅ ይናገራሉ። ‹‹ሰው ከስኬት ብቻ ሳይሆን ከውድቀትም ይማራል›› ሲሉም ከእሳቸው ስኬት ብቻ ሳይሆን ድክመትም ተነስተው ሌሎች ሴቶች የ‹‹ይቻላል›› መንፈስን በውስጣቸው በማዳበር ለስኬት የሚያበቃቸውን ምክር በመለገስ ያካፈሉንን ሀሳብ ቋጭተውልናል። እኛም ቀጣይ በሌላ ጽሑፍ ለመገናኘት ፈጣሪ የሳምንት ሰው ይበለን በማለት ለዛሬው ያዘጋጀነውን በዚሁ ቋጨን። ቸር እንሰንብት።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**በዛሬው ሳምንታዊው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1962 ዓ.ም ከወንጀልና ፀጥታ ጋር በተያያዘ የተሠሩ ዘገባዎችን ይዘን ቀርበናል፡፡ ዘገባዎቹ እንዲህም ይደረግ ነበር እንዴ የሚያሰኙና በአቀራረባቸውም ወጣ ያሉ በመሆናቸው አንባቢን ይስባሉ ብለን ነው ይዘናቸዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

### በሲዳሞ ተገደለች የተባለች ሴት በሕይወት ተገኘች፤ በዚህ ምክንያት 33 ሰዎች ታስረው ነበር

አዋሳ (ኢ/ዜ/አ/) ተገድላለች በመባል ፴፫ ሰላማውያን ሰዎች ያስከሰሰችው ሒዶ ጉራሮ የተባለችው ሴት በሕይወት ተገኘች፡፡

ሒዶ ጉራሮ በሰው እጅ ሕይወቷ አልፏል የተባለው በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ጦሎ ቦቶ ቀበሌ ግንቦት ፲፯ ቀን ፷ ዓ/ም/ ሲሆን ፤ጉዳዩን በመመርመር ላይ ለሚገኘው አዋሳ ከተማ ያስቻለው ከፍተኛው ፍ/ቤት ፪ኛ ወንጀል ችሎት በሕይወት መኖሯን በማረጋገጥ የጽሑፍ ማመልከቻ ያቀረበችው ታኅሳስ ፳፬ ቀን ፷፪ ዓ/ም ነው፡፡

አቶ ሶሬ ቦጬ የተባለው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፴፮/ ፭፻፳፫ መሠረት ፴፫ ሰዎች በመተባበር ባለቤቱን ሒዶ ጉራሮን በጦር መሣሪያ በማስፈራራት ደብድበው ከገደሉ በኋላ ፮ሺህ ፪፻፷ ብር ግምት ያላቸው የቀንድ ከብትና ሌላም ንብረት ፤እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የነበረውን ፪ሺህ ፭፻ ብር ጥሬ ገንዘብ በመውሰድ የሰው መግደልና የዘረፋ ወንጀል መፈጸማቸውን ያመለክታል፡፡

፴፫ ሰዎች የዝርፊያና የሰው መግደል ወንጀል ለመፈጸማቸው በሐሰት ማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ ፤ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀዳሚ ምርመራ ጉዳዩ እንዲጣራ ስለታዘዘ፤በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር ፹ መሠረት ክሱ ተከፍቶ ከተከሰሱት ፴፫ ሰዎች መካከል ፱ ሰዎች ተይዘው በወህኒ ቤት እንዲቆዩ ተደረገ፡፡ የቀሩት ፳፬ ሰዎች በመፈለግ ላይ እንዳሉ ሞተች የተባለችው ሴት « በተባለው ቀን ጨርሶ በዚያ አገር የለሁም ፡፡በፈቃድ ወደ ዘመዶቼ ሔጄ ነበር » በማለት ማመልከቻዋን ይዛ አዋሳ ከተማ ያስቻለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፪ኛ ወንጀል ችሎት ታኅሳስ ፳፬ ቀን፲፱፻፷፪ ዓ/ም ቀርባ አመለከተች፡፡

ከአሁን በፊት በቀዳሚ ምርመራ በሐሰት ከመሰከሩት ሰዎች መካከል አቶ ሻርጃ ሾራ ቀርቦ በሰጠው ቃል «ከዚህ በፊት ሞታለች ብዬ የመሰከርኩት ሴት ይህቺ ናት፡፡ አስቀድሜም አውቃታለሁ አብረንም በጉርብትና ብዙ ኖረናል፡፡ ነገር ግን ከሳሹ ጠጅ ጋብዞ በሐሰት እንድመሰክርለት ስለጠየቀኝ መሰከርኩ እንጂ ስትገደል አላየሁም » በማለቱ የፍርድ ውሳኔ እስኪሰጥ በወህኒ ቤት እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ የቀሩት ፪ ምስክሮች አቶ ጊጋ ፋላስና አቶ እሬቦ ኖቲ የተባሉት ጠፍተው በመፈለግ ላይ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በ፴፫ ሰዎች ላይ በሐሰት ክስ ያቀረበው አቶ ሶሬ ቦጬ በመጥፋቱ በመፈለግ ላይ መሆኑን አንድ የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ ገለጠ፡፡

**(ጥር 6 ቀን 1962 ዓ.ም)**

### ፈቃድ የሌላቸው የጦር መሣሪያ ነጋዴዎች ተቀጡ

አርባ ምንጭ (ኢ/ዜ/አ/)፡- ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ ሲነግዱ የተገኙት አራት ሰዎች እያንዳንዳቸው ፬፻ ብር ተቀጡ ፡፡

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የጦር መሣሪያ ሲነግዱ የተገኙት ቢርመጫ ኢላላ፤አስጨናቂ ወንድሙ ፤ደመቀ አድነውና ዓለሙ ዘነበ የተባሉት ተከሳሾቹ ሁለት ረጃጅም አልቤንና አንድ ምንሽር ጠብመንጃ ለሰዎች ለመሸጥ ሲያስማሙ፤በፖሊስ መከታተል የተያዙት ጥቅምት ፱ ቀን ፷፪ ዓ.ም ነው፡፡ እነ ቢርመጫ በዚህ አፈጻጸማቸው አርባ ምንጭ ሒያ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሰው ከቀረቡ በኋላ ፤አድራጐታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ እያንዳንዳቸው ፬፻ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ተበይኖባቸዋል፡፡

እንዲሁም በእጃቸው የተገኙት ጠብመንጃዎች በውርስ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆኑ ፤በተጨማሪ መወሰኑን ሻምበል ባሳድነው ባማው የአርባ ምንጭ ምድብ ዙሪያ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ገልጠዋል፡፡ በተከሳሾቹ ላይ ይኸው ቅጣት የተወሰነው ከትናንት በስቲያ ነው፡፡

**(ጥር 6 ቀን 1962 ዓ.ም)**

### 564 ልዩ ልዩ ጥይቶች ይዞ የተገኘው 50 ብር ተቀጣ

ባህርዳር (ኢ-ዜ-አ)፡- 564 ልዩ ልዩ ጥይቶች ይዞ የተገኘው ሰው 50 ብር ተቀጣ ፡፡ ዓለሙ ደስታ የተባለው ይኸው ሰው ፩፻፺፪ የካርባን ፫፻፸፪ የወጨፎ ጥይቶችን ይዞ ከአዲስ አበባ ወደ ባህርዳር ሲጓዝ የተያዘው ባለፈው ታኅሳስ ፳፫ ቀን ፷፪ ዓ.ም/ በመራዊ ከተማ ነው፡፡

ዓለሙ በዚህ አድራጎቱ ተከስሶ መየጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ፶ ብር መቀጫ እንዲከፍል ተበይኖበታል ፡፡ በእጁ የተገኙትም ጥይቶች ለመንግሥት ገቢ እንዲሆኑ መወሰኑን ሕግ አስከባሪው ወታደር ብርሃኑ ተገኝ ገልጠዋል፡፡

**(ጥር 22 ቀን 1962 ዓ.ም)**

### ጨለማን ተገን እያደረጉ ድብደባና ዘረፋ የሚፈጽሙ አርባ ሰዎች ተያዙ

አዲስ አበባ (ኢ-ዜ-አ-) የአዲስ አበባ ፖሊስ ረዳት ዋና አዛዥ ኰሎኔል አድማሱ ሀብተማርያም፤ ትናንት ከጧቱ ፬ ሰዓት ላይ ፤ሰሞኑን ጨለማን ተገን እያደረጉ በሰላማዊ ሰው ላይ ድብደባና የንብረት ዘረፋ አድርገዋል፤በመባል በፖሊስ መከታተል ስለተያዙት ፵ ሰዎች መግለጫ ሰጡ፡፡

ስለነዚሁ ሰዎች ገለጣ ባደረጉበት ጊዜም ፤የአዲስ አበባ የወንጀል ምርመራ ዋና ሹም ሌተናል ኰሎኔል ሥዩም ጨፍቄ ተገኝተው፤ፖሊሶቹ ወስላቶች ናቸው የተባሉትን በእንዴት ያለ ታክቲክና ዘዴ ደርሰው እንደያዙዋቸው አስረድተዋል፡፡

ከተያዙት ፵ ወስላቶች መካከል ፳፰ቱ ጉዳያቸው ተጣርቶ ፍርዳቸውን የሚጠባበቁ ሲሆን ፤ወንጀል የፈጸሙበትን ሥፍራና ቀበሌ በመምራት ማሳየታቸውንም ጭምር ሌተናል ኰሎኔል ሥዩም ጨፍቄ የአዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ዋና ሹም ገልጠዋል፡፡

ኰሎኔል አድማሱ ሀብተማርያም የአዲስ አበባ ፖሊስ ረዳት ዋና አዛዥ ስለተፈጸመው የወንጀል ሥራ በዝርዝር ሲያስረዱ፤«የወንጀሉ አፈጻጸም በዝቶ የተገኘው በቂርቆስ ቀበሌና የጎጃም በረንዳ በተባለው አካባቢ ሲሆን እስካሁን በተደረገው ጥብቅ ቁጥጥርና መከታተል ወንጀለኞቹ እጅ ከፍንጅ ተይዘው ሁሉንም በመሰብሰብ ለማዕከላዊ የወንጀል አሻራ ክፍል አስረክበናል» ብለዋል፡፡

ጉዳያቸው ተጣርቶ ለፍርድ ይቀርባሉ ከተባሉት ሰዎች መካከል ፲፰ቱ የተያዙት በአዲስ ከተማ ሲሆን ፲፫ቱ ደግሞ በቂርቆስ ቀበሌ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም የወንጀል ምርመራ ክፍል ዋና ሹም ሲገልጡ ፤ወንጀል የተፈጸመባቸው ሥፍራዎች ከዱሮ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ከልዑል መኰንን ት/ቤት ፊት ለፊት ያለው ቦታ ቁጭራ አቶ ሁሴን በረንዳ አጠገብ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በረንዳ አጠገብ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይ አዲሱ ከተማ ቁጭራ ሠፈርና እህል ተራ «ጎጃም በረንዳ» የሚባለው ሠፈር፤ አባኮራን ሠፈር መሆናቸውን ገልጠዋል፡፡

እንዲሁም አርበኞች መንገድ ዮሐንስ ቤ/ክ ፊት ለፊት የድሮ አባዲና ፖሊስ ማቋረጫ ራስ ደስታ ሆስፒታል «ሐምሌ 16 አጠገብ» እሪ በከንቱ ድልድይ ናዝሬት መኪና ተራ ደብረ ዘይት መንገድ መስከረም ቡና ቤት ኦርማ ጋራዥ አካባቢዎች ይገኙበታል፡፡

ወንጀሉን ፈጽመዋል በመባል ወጣቶች ቢያዙም ንብረት የጠፋባቸው ንብረታቸውን ለመውሰድ ቀርበው ባለመጠየቃቸው ኰሎኔል መገረማቸውንና ወደፊት እየቀረቡ እንዲወስዱ አሳስበዋል፡፡

**(የካቲት 21 ቀን 1962 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## የሩስያ ኃይሎች በምስራቅ ዩክሬን በኩል የማጥቃት ዘመቻቸውን ማፋፋማቸው ተነገረ

አዲስ አበባ፣ የሩስያ ኃይሎች በምሥራቃዊ ዩክሬን በኩል የሚያደርጉትን የማጥቃት ዘመቻ እንደገና አጠናክረው መቀጠላቸው ተነገረ።

ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ የዘለቀውና 46ኛ ቀኑን የያዘው የሩስያ እና የዩክሬን ጦርነት በዛሬው ዕለት በዩክሬን ምሥራቃዊ ግዛት በኩል እየተፋፋመ መምጣቱ እየተዘገበ ነው።

ዩክሬን በምሥራቃዊ ግዛቶቿ በኩል ከሩስያ ኃይሎች የሚሰነዘርባትን ጥቃት ለመመከት ኃይሏን እያሰባሰበችና በአካባቢው የሚገኙ ሰላማዊ ሰዎችን ከስፍራው የማስወጣት እንቅስቀሴዋን መቀጠሏን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

እንደ መገናኛ ብዙኃኑ ዘገባ፥ በዛሬው ዕለት የሩስያ ብረት ለበስ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ወደ ምሥራቃዊቱ ከተማ ካርኪቭ እየተተኳኳዙ መሆናቸውን የሳተላይት ምስሎችና የዩክሬይን ወታደራዊ ምንጮች አረጋግጠዋል።

ከትናንት ወዲያ የሩስያ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ከካርኪቭ በስተምሥራቅ በኩል ከሩስያ ድንበር አካባቢ በቅርበት ወደምትገኘው ቫልኪ ቡርሉክ ከተማ እየተመሙ እንደነበርም የሳተላይት ምንጮችን ዋቢ አድርገው መገናኛ ብዙኃኑ ዘግበው ነበር።

በዛሬው ዕለት ደግሞ የሩስያ ኃይሎች ተጨማሪ ተዋጊ ዩኒቶችን ( አሃዱዎችን) በማንቀሳቀስ ካርኪቭ ውስጥ ኢዙም በተሰኘ ቦታ የሚገኘውን የዩክሬይን መከላከያ ኃይል ሰብረው ለመግባት እና ማሪዩፖል ከተማን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር እየሞከሩ መሆናቸውን ነው የዩክሬይን ወታደራዊ ባለስልጣናት ስለጥቃቱ ባወጡት መግለጫ ያረጋገጡት።

ድርስ ካርኪቭን በከፊል በሩስያ ጦር ስር ለማዋል እየተካሄደ ባለው ውጊያ ከተማዋ በከባድ መሣሪያዎች እየተደበደበች መሆኗን ከዩክሬን ጦር ኃይሎች የወጡ መረጃዎች አመላክተዋል።




ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ “የአገሪቱ ምሥራቃዊ ክፍል እያጋጠመን ያለውን ከባድ ጦርነት ለመፋለም ዝግጁ ነን “ እያሉ ነው።

ፕሬዚዳንቱ በሩስያ ላይ የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ እንዲጣል እየወተወቱ ሲሆን፥ ለአገራቸው ሕዝብ ባደረጉት ንግግር “ከእንግዲህ የምንጠብቀው ጊዜ የለም፤ ሩስያ የምትተማመንበት የነዳጅ ገቢ ምንጭ መቆረጥ አለበት” በማለት ማዕቀቡ እንዲፋጠን ምዕራባውያን አጋሮቻቸውን ተማጽነዋል።

በሌላ በኩል የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን፥ አገራቸው ለዩክሬን የምታደርገውን የጦር መሳሪያ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንደምታጠናክር ቃል ገብተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን “ የትግል አጋርነትን ለማሳየት የተደረገ ነው “ ባሉት በዩክሬኗ ዋና ከተማ ኪየቭ ትናንት ባደረጉት ድንገተኛ ጉብኝት፥ 120 ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችንና አዳዲስ ፀረ-ሚሳኤል መሳሪያዎችን ለዩክሬን መንግሥት ለመስጠት ተስማምተዋል።

በተመሳሳይ የአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ዋና ኃላፊ ጆሴፍ ቦሬል ዛሬ በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ፥ “ ዩክሬን እንደገና ታንሰራራለች፥ ጠንክራም ትወጣለች” ካሉ በኋላ ፥ ለዩክሬናውያንም “ የአውሮፓ ኅብረት በመንገዳችሁ ሁሉ ከጎናችሁ ነው” ብለዋቸዋል።

የሩስያ ኃይሎች በምስራቁ የዩክሬን ግዛት በኩል የጀመሩትን ዘመቻ እያቀጣጠሉ በመጡበትና የሉሃንስክ ክልልን ቀለበት ውስጥ ባስገቡበት በአሁኑ ሰዓት ነዋሪዎቹ አካባቢያቸውን ለቅቀው እንዲወጡ ጥሪ ተላልፎላቸዋል።

በዚህም መሠረት ለነዋሪዎቹ መጓጓዣ በርካታ ባቡሮች ተመድበውላቸው ከተማዋን ለቅቀው እየወጡ ሲሆን፥ በዛሬው ዕለት ሁሉም የከተማዋ ነዋሪዎች ለቅቀው ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የሩስያ ጦር ዛሬ ማለዳ ላይ ሉሃንስክ እና ዲኒፕሮ በተባሉት የዩክሬን ክልሎች ላይ የከባድ መሳሪያ ጥቃት እንደተፈጸመም ተገልጿል።በዚህም ትምህርት ቤቶችና በርካታ ሕንፃዎች መውደማቸው እንዲሁም የሰው ሕይወት ማለፉን ዘጋርዲያን ጋዜጣና ሌሎች የዜና ምንጮች ዘግበዋል።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ለአገራቸው ሕዝብ ባደረጉት ንግግር፥ “ይህ ጦርነት ከባድ ቢሆንም በድል እንደምናጠናቅቀው እምነት አለን፤በአንድ በኩል እየተዋጋን፥ በሌላ በኩል ጦርነቱ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ዝግጁ ነን “ ብለዋል።

በተመሳሳይ ዩክሬን በኢኮኖሚ ሚኒስትሯ ዩሊያ ስቪሪደንኮ በኩል ዛሬ እንዳስታወቀችው፥ ለሩስያ በዓመት 6 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ እንደሚያስገኝ የሚገመተውን ከሩስያ የምታስገባውን የሸቀጦች ንግድ ሙሉ በሙሉ አግዳለች።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሯ ኢሪያና ቬሬስቹክ በበኩላቸው ዛሬ በሰጡት መግለጫ ፥ አገራቸው ሰላማዊ ዜጎች የጦርነት አካባቢዎችን ለቅቀው የሚወጡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ዘጠኝ የሰብዓዊ አቅርቦት መተላለፊያ መንገዶችን ከፍት ለማድረግ መስማማቷን አስታውቀዋል።

የሩስያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በተደጋጋሚ እንዳስታወቁት፥ “የዩክሬን መንግሥት በሩስያውያን ላይ የዘር ጭፍጨፋ ከማድረግና ዓለምአቀፍ ሕግን በመጣስ የምዕራባውያን ተላላኪ በመሆን የአገሪን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ከሚጥል ድርጊቷ ካልተቆጠበች በስተቀር ዘላቂ ሰላም ሊመጣ ፥ ውጊያውም ሊቆም አይችልም” የሚል አቋም ነው ያላቸው።

በሌላ በኩል የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ” ሩስያ በቀጣይ ልታደርግ የምትችለውን ወታደራቂ ጥቃት ለመከላከል ያስችለኛል” የሚለውን በዩክሬን ድንበር ላይ ያለውን ወታደራዊ ይዞታ የማጠናከር ዕቅድ እያዘጋጀ መሆኑን ነው ያስታወቀው።

የኔቶ ዋና ጸሐፊ ጀንስ ስቶልተንበርግ ከቴሌግራፍ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ፥ “የሩስያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ለፈጸሙት ድርጊት የረዥም ጊዜ ዋጋቸውን ሊያገኙ በሚችሉበት መሠረታዊ የሽግግር ጊዜ ላይ ነን፥ ለዚህም ወታደራዊ ኮማንደሮቻችን አማራጮችን እንዲያቀርቡልን ጠይቀናቸዋል“ ብለዋል።

ይህ የወታደራዊው ሹም ንግግር ምን ማለት እንደሆነና ዩክሬንና ሩስያ ጦርነት ወዴት እንደሚያመራ አሁንም እያነጋገረ ይገኛል።

# ስፖርት



## የተጫዋቹ የአዲስ አበባ ቆይታ

**ብርሃን ፈይሳ**

የአውሮፓ ታላላቅ የእግር ኳስ ክለቦች የሚፋለሙበት የሻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ በአዲስ አበባ የነበረውን የአንድ ቀን ቆይታ አጠናቆ ወደ ቀጣይ መዳረሻው አምርቷል:: በመላው ዓለም በሚገኙ 31 አገራት እየተዘዋወረ በደጋፊዎች ሲጎበኝ ቆይቷል፤ ዋንጫው በአፍሪካ መዲና አዲስ አበባም ሰሞኑን ተገኝቷል::

ከዋንጫው ጎን ለጎን በሻምፒዮንስ ሊግ ታሪክ ከሶስት የተለያዩ ክለቦች ጋር አራት (ከአያክስ እና ሪያል ማድሪድ አንድ አንድ እንዲሁም ከኤሲሚላን ጋር ሁለት) ዋንጫዎችን በማንሳት ስሙን በስኬት መዝገብ ያጻፈው የቀድሞ ተጫዋችና አሰልጣኝ ክላረንስ ሴዶርፍ ከዋንጫው ጋር በአዲስ አበባ ተከስቷል፤ተጨዋቹ በተያዘለት መርሐ ግብር መሠረትም በእግር ኳስ ሕይወቱ የተገነዘበውንና ያገኘውን ልምድ ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ጠቁሟል::

ሆላንዳዊው ተጫዋች ለበርካታ ጊዜያት ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወር ኢትዮጵያን እንደመሸጋገሪያ ሆና እንደሚያውቃት ተናግሯል፤ አሁን ደግሞ አገሪቱን በአካል ለመጐብኘት በመብቃቱ የተሰማውን ደስታ አስታውቋል::

እግር ኳስንም ሆነ በየትኛውም ዘርፍ ሌሎችን ከመመልከት ይልቅ ራስን መሆንና በራስ መንገድ ለስኬታማነት ለመብቃት መጣር አስፈላጊ መሆኑን የተናገረው ተጫዋቹ፣ ሁሉም አገር የራሱ ባህልና ልምድ እንዳለው ሁሉ ክለቦችም የየራሳቸው መለያ እንዳላቸው ያመለክታል፤ እርሱ በጣሊያኖቹ ተቀናቃኝ ክለቦች ኢንተርሚላን እና ኤሲሚላን ክለቦች የተጫወተ ቢሆንም ሊያነጻጽራቸው እንደማይችል ግን ይጠቁማል:: በመሆኑም በራስ መንገድ ጥረት በማድረግ ስኬታማነት ላይ መድረስ እንደሚቻልም ነው አጽንኦት ሰጥቶ የገለጸው::

22 ዓመታትን በስድስት የሆላንድ፣ ስፔን፣ ጣሊያን እና የብራዚል ክለቦች ተዘዋውሮ በመጫወትና በሆላንድ ብሔራዊ ቡድንም ይታወቃል:: በአንድ ወቅትም ከዓለም ስመጥር የመሐል ሜዳ ተጫዋቾች መካከል አንዱ እና ከሻምፒዮንስ ሊጉ ምርጥ 20 ተጫዋቾች መካከል የነበረው ሴዶርፍ፤ በአውሮፓ ታላላቅ ክለቦች ለመጫወት ለሚሹ ወጣቶች መልዕክት አስተላልፏል::

በስፖርቱ ከፍተኛ ሕልም ያላቸው ወጣቶች ግባቸውን ለማሳካት እስከሚችሉ ማለማቸውን መቀጠል እንዳለባቸው ነው ያሳሰበው:: ይህም ብቻ ሳይሆን ከታላላቆቻቸው ድጋፍን መጠየቅና በሕይወታቸው ከሚገጥማቸው ልምድ መማር እንደሚኖርባቸውም አስገንዝቧል:: ህልምን እንደ መኖር መልካም ነገር የለምና ወጣቶች አላስፈላጊ ካልሆኑ ነገሮች በመራቅ ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ጠንክረው መሥራት አለባቸው ሲል አሳስቧል::

የተጫዋቹንና የሻምፒዮንስ ሊጉን ዋንጫ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ተከትሎም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጅራ መልዕክት አስተላልፈዋል:: በንግግራቸውም ሃይንከን የቻምፒዮንስ ሊጉ ስፖንሰር መሆኑን ጠቅሰው፣ በኢትዮጵያም የአትሌቲክስ እና እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ጋር ጠንካራ ሥራ በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል:: እንደማሳያም በአራት ዓመት ውስጥ 56ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የእግር ኳስ ፌዴሬሽንን ስፖንሰር ማድረጉን ጠቅሰዋል:: አሁንም ታች ወርዶ በተለይ በታዳጊዎች ላይ በሚሠራበት ሁኔታ ላይ ውይይት እየተደረገ መሆኑንም ተናግረው፣ ተቋሙ ከፌዴሬሽኑ ጋር በሚሠራው በዚህ ሥራም ከፍተኛ ክብርና ምስጋና ይገባዋል::

የተጫዋቹን መምጣት ተከትሎ ከተያዘው መርሐ ግብር መካከል አንዱ ከ20 ዓመት በታች ቡድን ጋር




በመሆን መጫወት ነበር:: ፕሬዚዳንቱ፤ እግር ኳስ መጫወትን ራዕያቸው ያደረጉ ታዳጊዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ እንደ ክላረንስ ሲዶርፍ ካሉ ተጫዋቾች ጋር ሲገናኙ እንዲሁም ለጥቂት ደቂቃዎች አብረው የመጫወት ዕድል ሲያገኙ ተስፋን ይጭርባቸዋል ይላሉ:: በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውስጥ እነ ኃይሌ እና ደራርቱን የመሳሰሉ አትሌቶችን እያዩ ሌሎች እንደወጡት ሁሉ ምሳሌ የሚሆናቸው ሰው መሆኑንም በመጥቀስ፣ በየዓመቱ ተቋሙ ለሚያደርገው ለዚህ ተግባሩ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስም አመስግነዋል::

አቶ ኢሳያስ የአፍሪካ ዋንጫ እንደ ሻምፒዮንስ ሊጉ ዋንጫ ሁሉ በመላው ዓለም የሚታይበትን ጊዜ እንደሚናፍቁም ጠቁመዋል:: ይህ እንዲሆን ደግሞ አፍሪካውያን ጠንክረን መሥራት እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የእግር ኳስ ኮከብ ለማየት ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑንም ነው የጠቆሙት::

ሃይንከን ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ ስኬታማ የሆኑ ተጫዋቾችን እንደ ብራዚላዊው የእግር ኳስ ጠቢብ ሮናልዲኒሆ ጎቾ እንዲሁም ፈረንሳዊውን የቀድሞ ተጫዋች ክላውድ ማካሌሌን ከአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ ጋር ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣት ከአድናቂዎቻቸው ጋር ማገናኘቱ ይታወሳል::

## ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# መቻልን በተግባር ያሳዩ ጀግኒቶች

**ቤዛ እሸቱ**

በጉራጌ ዞን እንደጋኝ ወረዳ የሚገኙ ሴቶች ከእናት የሚበልጥ ምንም የለም ሲሉ የልማት ቡድናቸውን አዶ ዳሻ (እናቴ አንቺ ነሽ) ሲሉ ሰይመውታል:: በባህር ዳር ከተማ በአገር አቀፍ ደረጃ ጥሩ የሠሩ የልማት ቡድኖች በተሸለሙበት መድረክ ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ተመርጠው ሽልማት ሲቀበሉ ያገኘናቸው ወይዘሮ አምሳል ሽብሩ፣ ከመሬቱ ብዙ ነገር ስለምናገኝ እናታችን ናት ብለን ነው ስም ያወጣንላት፤ ከእናት መቼም የሚበልጥ ነገር የለምና ይላሉ::

29 አባላት ያሉት የልማት ቡድን የተመሠረተው ምንም ገቢ ባልነበራቸውና የትዳር አጋሮቻቸውን እጅ ይጠብቁ በነበረ የቤት እመቤቶች ነው:: ምንም የሌለንና ከጓዳ ያልወጣን ነበርን የሚሉት ወይዘሮ አምሳል፣ የልማት ቡድኑ መነሻ ቁጠባ መሆኑን ይገልጻሉ:: ገበያ ሲሄዱ ከምናጠፋው ለምን ቀንሰን አንቆጥብም በሚል በሳምንት ሁለት ብር ማጠራቀም የቁጠባቸው መነሻ ነበር:: በሁለት ብር የተጀመረው ቁጠባ መጠራቀም ሲጀምር ይሄንን ብር ከምናጠፋው ለምን አብረን አንሠራም ወደሚል ሀሳብ አደገ::

የተጠራቀመው ብር መጥፋት የለበትም፤ እኛም ሁሌ የባሎቻችንን እጅ ማየት የለብንም፤ በራሳችን ሥራ መሥራት አለብን ብለው ተነሱ:: በዚህም ለቀበሌያቸው ያቀረቡት መሥሪያ ቦታ ይሰጠን ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ 54 ሄክታር መሬት አግኝተዋል:: ከዚህ ውስጥ 34 ሄክታሩ መሬት የሚለማ ነው:: አባላቱ በጋራ በመሆን በበልግ ወቅት ድንች በመሐር ስንዴን ያመርታሉ:: ያመረቱትን ከሌሎች ማኀበራት ጋር በመዋዋል ይሸጣሉ:: ምንም እንኳን ሀሳባቸው በዓመት ሦስት ጊዜ ለማምረት ቢሆንም፤ በአካባቢው የውሃ ችግር መኖሩ መስኖ መጠቀም ስላላስቻላቸው ምርታቸው በዓመት ሁለቴ እንዲወሰን አድርጎታል::

በፊት የባሎቻችንን እጅ የምናይ ልጆቻችንን እንኳን



**ወይዘሮ ሳዶፌ ሱሬ ሽልማት ሲቀበሉ**

ማስተማር የማንችል ነበርን የሚሉት ወይዘሮ አምሳል፣ እዚህ የልማት ቡድን ውስጥ ከገባን በኋላ ብዙ ነገሮችን ተምረናል ይላሉ:: በሕይወታቸው የታየውን ለውጥም ሲናገሩ “ከዚህ በፊት በኩራዝ ስንጠቀም ነበር አሁን ግን በሶላር እንጠቀማለን፤ በፊት ነፍሰ ጡር ሆነንም በማገዶ ጭስ እየታፈንንና እየተቃጠልን ስንጋግር ነበር:: አሁን ግን ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ስለምንጠቀም ምንም ጭስና እሳት አይነካንም፤ልጆቻችንን እስከ ዩኒቨርስቲ ልከን እያስተማርን ነው›› ብለዋል”

የልማት ቡድኑ አባል የሆኑት ከማኅበር አካውንት በተጨማሪ ሁሉም አባላት የግል አካውንት አላቸው:: በዚህም ከዚህ ቀደም የነበረውን በዓል ሲመጣ ከባሎቻቸው ጋር የነበረውን ብር ስጠኝ አልሰጥም ጭቅጭቅ መቅረቱንና ከራሳቸው አልፎ ለቤተሰቦቻቸው መትረፋቸውንም ያጠቅሳሉ::

ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ያፈራው የልማት ቡድን አባላት አሁን ሀሳባቸው በአመት እንዴት ሦስቴ እናምርት እና በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያ ታግዞ ስለማምረት ነው:: አሁን ቴክኖሎጂ ረቅቋል የሚሉት ወይዘሮ አረጋሽ፣ የሚያስፈልገንን ነገር ከዚህ ቀደም ግብርናው እስኪመጣ ድረስ ብዙ ነገር ይጨንቀን ነበር፤ አሁን ግን በስልክ እንጠራቸዋለን ወዲያው ስለሚመጡ የሚያስፈልጋቸውን ግብአት ከእነሱ ጋር በመነጋገር እንደሚሠሩም ያስረዳሉ::

ወይዘሮ ሳዶፌ ሱሬ፣ የሚመሩት በሲዳማ ክልል ሁላ ወረዳ ጨልቤሳ ቀበሌ የሚገኘዉ አዳልቾ (ብሩክ) ልማት ቡድን በመደራጀት ከወንድ ጥገኝነት ተላቀው እራሳቸውን መቻል በፈለጉ 25 ሴቶች የተመሠረተ ነው:: ያላቸውን ከመቆጠብ የተጀመረው የልማት ቡድን የተጠራቀመው 35ሺ ብር ሲደርስ ከዛ ላይ የተወሰነ በማንሳት ሁለት በግ በመግዛት የንግዱን ዓለም ተቀላቀሉ:: በዚህ ሳይወሰኑ መሬት በመኮናተር ወደ ግብርናው መስክ የዘለቁ ሲሆን፣ በተኮናተሩት መሬት ድንችና ሰንዴ ያመርታሉ:: እንደ በፊቱ የወንድ እጅ ማየታችን ቀርቶ አሁን የኛን ለውጥ ስላዩ ወንዶቹም አባል እንሁን ማለታቸውን ወይዘሮ ላዶፌ ያስረዳሉ:: የማኅበሩን ተቀማጭ በማሳደግ ለከርሞ መኪና መግዛትን ያልማሉ::

ቁጠባ ስንጀምር እንደቀልድ ነው የሚሉት ደግሞ ወይዘሮ ጅዳ መሐመድ፣ የነዊታ የገንዘብና ቁጠባና ብድር ማኅበር ሰብሳቢ ናቸው፤ ማኅበሩ ከቤኒሻንጉል ክልል የተሻለ አፈጻጸም በማሳየቱ ማኅበራቸውን ወክለው ሽልማት ወስደዋል:: የቁጠባ ማህበሩ በ2003 ዓ.ም ሲጀመር በ20 ሴቶች ነው፤ ከአባላቱ ግማሹ በወር ዘጠኝ ብር ሲቆጥቡ አስሮቹ ደግሞ 20 ብር በመቆጠብ የተቋቋመ ነው:: ለውጥ መታየት የጀመረው 20 ሺ ብር ማኅበሩ ተበድሮ ለአባላቱ እንደቆጠቡት መጠን ካበደረ በኋላና የወለድ ክፍፍሉን ተከትሎ የአባላት ቁጥር መበራከቱን ጠቅሰዋል:: አሁን የማኅበሩ የተቀማጭ መጠንም ሆነ አባላት በየጊዜው የሚቆጥቡት መጠንም ያደገ ሲሆን፣ የአባላቱ መጠንም ወደ 120 ከፍ ብሏል::

ቁጠባው ሲጀመር እኔ እራሱ እንደቀልድ ነው ያየሁት የሚሉት ወይዘሮ ጅዳ፣ ከቁጠባ በመበደር ሰላሳ ቆርቆሮ ቤት እንደሠሩ ነግረውናል:: በአካባቢው የተነሳውን ግጭት ተከትሎ አብዛኛው ኅብረተሰብ ስጋት ስላደረበት የቁጠባ ማኅበሩ አባላትም ፍራት እየተሰማቸው መቆጠብ አልቻሉም:: በዚህም ያለፉትን ሁለት ወራት አባላት እየቆጠቡ አለመሆኑን ይገልጻሉ::

ወይዘሮ አመለወርቅ ኤፍሬም፣ በአማራ ክልል ደብረኤልያስ ወረዳ የሚገኘው ወይርማ የልማት ቡድን መሪ ናቸው:: ከአማራ ክልል የተሻለ አፈጻጸም በማሳየቱ ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለልማት ቡድኑ የተበረከተውን ሽልማት ወስደዋል:: የማኅበሩ አባላት ከአካባቢው አስተዳደር የተረከቡትን መሬት በማረስ ቤታቸውን ይደግፋሉ፤ እርስ በእርስም ይማማራሉ:: በፊት ልጆች ትምህርት ቤት አንልክም እንል የነበረው ተገናኝተን መመካከር ስንጀምር የሌሎች ልጆችም እንዲሄዱ የምንመክር ሆነናል ይላሉ:: በልማት ቡድኑ ልጆች በበቂ ክትትል እንዲማሩ፣ ነፍሰ ጡር እናቶች ወደ ጤና ተቋም እንዲሄዱ ይሠራል::

አራቱም ጀግኒቶች ለሴቶች መልእክታቸው ተመሳሳይ ነው:: “አንችልም ማለት ቀርቶ እንችላለን ብለን ከተነሳን ሁሉን ነገር መሥራት እንችላለን እንበርታ” ይላሉ::